መልእክተ፡ ያዕቆብ፡ ሐዋርያ፡ እኁሁ፡ ለእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ።

የያዕቆብ፡ መልእክት ።

ያዕቆብ፡ ከገድሉ፡ ጽናት፡ የተነሣ፡ ወ
ኮነ፡ እግሩ፡ ከመ፡ እግረ፡ ገመል፡ ይለ
ዋል፤ እግሩ፡ እንደ፡ እግረ፡ ገመል፡ ሁኖ፡
ይኖር፡ ነበር፤ ሐዋርያት፡ ለስብከተ፡ ወን
ጌል፡ አይፋጠንም፡ ብለው፡ በኢየሩሳ
ሌም፡ ኤጲስ፡ ቆጶስነት፡ ሹመውት፡ ሂደ
ዋል፡ ይህስ፡ ሐዋርያ፡ ደመና፡ ጠቅሶ፡
ካሰበው፡ ደርሶ፡ ብዙ፡ አስተምሮ፡ አሳ
ምኖ፡ ይውል፡ እንጅ፡ የለ፡ በዚያውም፡
ላይ፡ ከሐዋርያት፡ ሁሉ፡ አንድ፡ አንድ፡
ደዌ፡ የሌለበት፡ የለም፡ ጴጥሮስን፡ ወ
ኮነ፡ ድውየ፡ ሥጋ፡ ይለዋል፡ ጳውሎስም፡
ተውህበኒ፡ መልአከ፡ ሰይጣን፡ ዘይደጕ
ጽኒ፡ ሥጋየ፡ ወይኰርዐኒ፡ ርእስየ፡ ይለ
ዋል፡ ብሎ፡ በኢየሩሳሌም፡ የነበሩ፡ አይ
ሁድ፡ ምሁራን፡ አራት፡ ነበሩ፡ እሱም፡
ምሁረ፡ አሪት፡ ነበረና፡ ከእሱ፡ በቀር፡
ሌላ፡ የሚያውቅባቸው፡ የለም፡ ብለው፡
ያገሩን፡ ስርዶ፡ ባገሩ፡ በሬ፡ እንዲሉ፡
ከዕለታት፡ ባንድ፡ ቀን፡ ምሥጢረ፡ ሥጋ
ዌን፡ አምልቶ፡ አስፍቶ፡ ሲያስተምር፡
አንድ፡ አይሁዳዊ፡ ሰምቶ፡ በምንፃበ፡
ዕፀ፡ ራሱን፡ መቶ፡ ገሎታል፤ ከዚያ፡ አስ
ቀድሞ፡ ሲያጸና፡ ጽፎ፡ ይልክላቸዋል ።
(ምክንያት)፡ ኦ፡ አኃው፡ ኩኑ፡ በኵሉ፡
ፍሥሐ፡ በል፡ ም፡ ፩፡ ፪። ወትዕግሥትሰ፡
ፍጹም፡ ግብር፡ በል፡ ፬። ወእመሰ፡ ቦ፡
ዘኀጥአ፡ ለጥበብ፡ በል፡ ቍ፡ ፭። ለይትመው
ካሕ፡ እኁነ፡ ነዳይ፡ በል፡ ቍ፡ ፱። ወእ
መቦ፡ ዘትሜክር፡ ኢይበል፡ እግዚአብ
ሔር፡ በል፡ ቍ፡ ፲፫። ወይኩን፡ ኵሉ፡
ብእሲ፡ ፍጡነ፡ ለሰሚዕ፡ ወጕንዱየ፡
ለነቢብ፡ በል፡ ቍ፡ ፲፱። አኀዊነ፡ ኢት
ኩን፡ ለገጸ፡ ሰብእ፡ ሃይማኖትክሙ፡ በል
ም፡ ፪፡ ፩። እኁሁ፡ ለእግዚእነ፡ አለው፤
አይሁድ፡ ወልደ፡ ዮሴፍ፡ ብለውታልና፡
ይህማ፡ እሱስ፡ እንደ፡ አይሁድ፡ ይሰድ
በዋልን፡ ብሎ፡ በተዘምዶተ፡ ሥጋ፡ እኁ
ሁ፡ አለው፡ መገናኛው፡ ጕንዱ፡ አላዛር፡
ነው፤ አላዛር፡ ማትያንና፡ ቅስራን፡ ይወ
ልዳል፡ ቅስራ፡ ኢያቄምን፡ ኢያቄም፡
እመቤታችንን፡ ማትያን፡ ያዕቆብን፡ ያዕ
ቆብ፡ ዮሴፍን፡ ዮሴፍ፡ ያዕቆብን፡ ይወ
ልዳል ። አንድም፡ እናቱ፡ በሕፃንነቱ፡
ሙታበት፡ እመቤታችን፡ ጡት፡ እያጠ
ባች፡ አሳድጋዋለችና፡ ሐሊብ፡ ድንግል
ናዊንስ፡ ካንድ፡ ከጌታ፡ በቀር፡ የጠባው፡
የለም፡ ብሎ፡ እኁሁ፡ አለው፡ አብሮ፡
በማደግ፡ የያዕቆብ፡ ታሪኩ፡ ብዙ፡ ነው ።
በዬደጁ፡ ይተረካል ።

ምዕራፍ፡ ፩፡ ክፍል፡ ፩፡

፩፤ እምያዕቆብ፡ ገብረ፡ እግዚአብሔር፡ ወእግዚ
እነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ።

እግዚአብሔር፡ አብን፡ ጌታችን፡ ኢየሱ
ስ፡ ክርስቶስንም፡ ከማገለገል፡ ከኔ፡ ከያ
ዕቆብ፡ የመጣች፡ ክታብ፡

ለዐሠርቱ፡ ወክልኤቱ፡ ሕዝብ፡ ድዮስ፡ ጾራ፡

በዝርወት፡ ላሉ፡ ለአሥራ፡ ሁለቱ፡ ነገ
ደ፡ አምላክ፡ ትድረስላቸው፡ ድዮስ፡ ስመ፡
አምላክ፡ ነው። (ጥቅ)፡ ወአምጽኡ፡ ማሬ፡
ዘድዮስ፡ እንዲል፡ ካህነ፡ አምላክ፡ ሲል፡
ልበ፡ ድዮስ፡ እንዲል፡ ልበ፡ አምላክ፡
ሲል፡ ጾራ፡ ዝርወት፡ ማለት፡ ነው ። ጽር
ዮኒ፡ እንዲል፡ ወአኀለፎሙ፡ እንተ፡ ጽል
ንትዩም፡ ይላል፡

ሰላም፡ ለክሙ፡

ቸር፡ አላችሁን፡ ፩፡ ጴጥ፡ ፩፡ ፩ ።

፪፤ ኦ፡ አኃው፡ ኩኑ፡ በኵሉ፡ ፍሥሓ፡ ሶበ፡ መን
ሱት፡ ይመጽአክሙ፡ ዘዘዚአሁ፡

ወንድሞቻችን፡ በፍጹም፡ ደስታ፡ ጽኑ ።
አንድም፡ በፍጹም፡ ደስታ፡ ኑሩ፡ ኩኑ፡
ፍሡሐነ፡ በኵሉ፡ በውስጥ፡ በአፍአ፡
ደስ፡ ያላችሁ፡ ሁኑ፡ (ሶበ፡ መንሱት)፡
ዘዘዚአሁ፡ ብለህ፡ ግጠም፡ ልዩ፡ ልዩ፡
መከራ፡ በመጣባችሁ፡ ጊዜ፡ ኩኑ፡ ፍሡ
ሐነ፡ ላለው፡ ሮሜ፡ ፭፡ ፫ ።

፫፤ እንዘ፡ ተአምሩ፡ ከመ፡ መከራሃ፡ ለሃይማኖት
ክሙ፡ ትዕግሥተ፡ ይገብር፡ ለክሙ ።

የሃይማኖታችሁ፡ ፈተና፡ ተዓጋሥያን፡
እንዲያሰኛችሁ፡ አስበ፡ ትዕግሥትን፡
እንዲያሰጣችሁ፡ አውቃችሁ ።

፬፤ ወትዕግሥትሰ፡ ግብር፡ ፍጹም፡ ባቲ፡

ትዕግሥትኒ፡ ሲል፡ ነው፡ ትዕግሥትም፡
...(ጥቅ)፡ ዛቲ፡ ገድል፡
ትርፍት፡ ኢኮነት፡ አሐቲ፡ እንዲል ።

ከመ፡ ትኩኑ፡ ፍጹማነ ።

በገድል፡ ፍጹማን፡ ትሆኑ፡ ዘንድ ።

ወጥዑያነ ።

ከንዴተ፡ ገድል፡ ጥውያን፡ ትሆኑ፡ ዘንድ

እንዘ፡ አልቦ፡ ዘተነጥኡ

ከትሩፋተ፡ ሥጋ፡ ከትሩፋተ፡ ነፍስ፡
ምንም፡ ምን፡ ያልሠራችሁት፡ ሳይኖር ።
አንድም፡ እንዘ፡ ተአምሩ፡ ብሎ፡ ነበ
ረና፡ (ወትዕግሥትሰ)፡ ትዕግሥት፡ ትዕ
ግሥት፡ ትላለህ፡ እንጅ፡ ትዕግሥት፡
ምን፡ ቁም፡ ነገር፡ ናት፡ ትሉኝ፡ እንደ፡
ሆነ፡ ትዕግሥትስ፡ ፍጹም፡ ክብር፡ ናት፤
(አላት፡ ቢልም፡ አንድ፡ ነው፡ (ጥቅ)፡
ኀሩይኒ፡ ኢኮነ፡ እግዚእ፡ ግብር፡ እንዲል ።
(ከመ፡ ትኩኑ)፡ በክብር፡ ፍጹማን፡ ትሆ
ኑ፡ ዘንድ፡ (እንዘ፡ አልቦ)፡ ከክብረ፡
ሥጋ፡ ከክብረ፡ ነፍስ፡ ምንም፡ ምን፡
የምታጡት፡ ሳይኖር ።

፭፤ ወእመሰ፡ ቦ፡ ዘኀጥአ፡ ለጥበብ፡ ለይስአል፡
ኀበ፡ ወሀቢ፡ እግዚአብሔር፡ ዘይሁብ፡ ለኵሉ፡ በሲ
ፋሕ፡ እንዘ፡ ኢይትዔየር፡ ወኢይዘረኪ ።

ትዕግሥትን፡ ያጣት፡ ሰው፡ ቢኖር ።
(ጥቅ)፡ ልቡ፡ ለቁጡእ፡ ዕሩቅ፡ ውእቱ፡
እምሥጢራተ፡ እግዚአብሔር፡ ብእሲ፡
ነዊኅ፡ መንፈስ፡ ወርኁበ፡ ልብ፡ ጠቢብ፡
ውእቱ፡ እንዲል፡ ዕትሥ፡ ሲል፡ ነው ።
አንድም፡ ጥበብን፡ ያጣ፡ ሰው፡ ቢኖር፡
ለሁሉ፡ አምልቶ፡ አስፍቶ፡ አብዝቶ፡
ከሚሰጥ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ይለምን፡
ለይስአል፡ እንዘ፡ ኢይትዔየር፡ ሳያጣ
ጥል፡ ሳያፈናጥቅ፡ ወኢይዘረኪ፡ ሳይሳ
ደብ፡ ይለምን፡ (ጥቅ)፡ ዘርከየ፡ ለማር፡

www.ethiopianorthodox.org

ወቅሪስ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ ዘይሁብ ፡ እንዘ ፡ ኢይትዔየር ፡ ሳይላገድ ፡ ሳያጣ ጥል ፡ ወኢዘረኪ ፡ ሳይመካ ፡ ከሚሰጥ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይለምን ።

ወይትወሀብ ፡ ሎቱ ።

ይሰጠዋል ፡ ምሳ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ማር ፡ ፲፩ ፡ ፳፬።

፮ ፤ ወይስአል ፡ እንዘ ፡ ይትአመን ፡ ወኢይናፍቅ ።

ሳይጠራጠር ፡ አምኖ ፡ ይለምን ። አን ድም፡ ፤ (ኢይናፍቅ) ፡ አይጠራጠር ።

እስመ ፡ ዘይናፍቅሰ ፡ ይከውን ፡ ከመ ፡ ሞገደ ፡ ባሕር ፡ እንተ ፡ ይዘብጣ ፡ ነፋስ ፡ ወያነውጻ ።

የሚጠራጠር ፡ ሰው ፡ ነፋስ፡ እንደሚያወ ጣው፡ እንደሚያወርደው፡ እንደ፡ ባሕር ፡ አዝዋሪ ፡ ነውና፡ ኢይናፍቅ ፡ ላለው። አን ድም ፡ የሚጠራጠርስ ፡ ነፋስ ፡ እንደሚያ ወጣው ፡ እንደሚያወርደው ፡ እንደ ፡ ባ ሕር ፡ አዝዋሪ ፡ ነው ። (ሐተታ) ፡ እንደ ፡ ማውጣት ፡ እገኛለሁ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ማውረድ ፡ አጣለሁ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፯ ፤ ወኢይምሰሎ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ዘይ ነሥእ ፡ ምንተኒ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

ለዚያ፡ሰው፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ምን ም፡ ምን፡ የሚያገኝ፡ አይምሰለው ።አንድ ም፡ እንዳያገኝ፡ ይወቅ፡ አገኛለሁ፡አይበል፡

፰ ፤ ብእሲ ፡ ዘክልኤ ፡ ልቡ ፡ ሀዉክ ፡ ውእቱ ፡ በ ኵሉ ፡ ፍኖቱ ።

ዘክልኤ ፡ ልቡ ፡ በኵሉ ፡ ፍኖቱ ፡ ሀውክ ፡ ውእቱ ፡ በኵሉ ፡ ፍኖቱ ፡ (ግጥም) ፡ በሥ ራው ፡ ሁሉ ፡ ሁለት ፡ ልብ ፡ የሆነ ፡ በሥ ራው ፡ ሁሉ ፡ ይታወካልና ፡ (ሐተታ) ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይመስላል ፡ ቢሉ ፡ ከመ ንታ ፡ መንገድ ፡ ቁሞ ፡ በዚህን ፡ ልሂድ ፡ በዚህ ፡ ሲል ፡ ጊዜ ፡ መሸቶበት ፡ አውሬ፡ የተጣላውን ፡ ወንበዴ ፡ የቀጠቀጠውን ፡ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ይመስላል ፡ አንዱን ፡ ይዞ ፡ ቢሄድ ፡ ወይም ፡ ከዋሻ ፡ ወይም ፡ ከመ ንደር ፡ ያደርሰው ፡ ነበረና ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፳ ።

፱ ፤ ወለይትመካሕ ፡ እኁነ ፡ ነዳይ ፡ በተልዕሎቱ።

ከዚህም ፡ ባለጸጋና ፡ ድሀ ፡ በወንጌል ፡ አ ምነዋል ፤ ድሀው ፡ ቀድሞ ፡ ባለጸጋው ፡ ሲመጣ ፡ ይነሣለት ፡ ሲሄድ ፡ ይሸኘው ፡ ይከተለው ፡ ይፈታለት ፡ ይታጠቅለት ፡ የነበረ ፡ በወንጌል ፡ አንድ ፡ ከሆነ ፡ ብሎ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚያየው ፡ ሆኗል ፤ ባለጸጋ ውም ፡ አይቶ ፡ አሁን ፡ ይህ ፡ ድሀ ፡ ለእግ አብሔር ፡ ምን ፡ ተሁለት ፡ ይላል ፡ ጥሬ ፡ እራቱ ፡ ጭራሮ ፡ መብራቱ ፡ ቀድሞም ፡ ይኸው ፡ ዛሬም ፡ ይኸው ፡ ብሏል ፡ ድሀ ውም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ በወንጌል ፡ ካመኑ፡ በኋላ ፡ ድሀ ፡ ተብሎ ፡ መሰደብ ፡ አለን ፡ ብሎ ፡ አዝኗል ፡ ለዚህ፡ ያመጣል ፡ ድሀው፡ ወንድማችን ፡ ከከብት ፡ በመራቁ ፡ ደስ ፡ ይበለው፡(ጥቅ)፡ ከመ፡ንትመካሕ፡እንዲል። (ሐተታ) ፡ ተልዕሎ ፡ አላት ፡ ከከብት ፡ መራቅን ፡ ልዕልና ፡ ነፍስን ፡ የምታመጣ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ (ጥቅ) ፡ ነዳይሰ ፡ ግዑዝ ፡ ው እቱ ፡ ወይጌይስ፡ እምእለ ፡ የዐጥቁ ፡ ቅና ተ ፡ መንግሥት ፡ እንዲል ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፰ ።

፲ ፤ ወባዕልሰ ፡ በተትሕቶቱ ፡

ባለጸጋ ፡ ግን ፡ ከከብት ፡ ባለመራቁ ፡ እን ዳይመካ ፡

እስመ ፡ ከመ ፡ ፍሬ ፡ ሣዕር ፡ የኀልፍ ፡

ብዕል ፡ እንጅ ፡ እንደ ፡ ፍሬ ፡ ሣዕር ፡ ያል ፋል ። (ሐተታ) ፡ ተትሕቶ ፡ አላት ፡ ከከ ብት ፡ አለመራቅን ፡ ትሕትና ፡ ነፍስን ፡ የምታመጣ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩፡፳፬ ።

፲፩ ፤ እምከመ ፡ ሠረቀ ፡ ፀሐይ ፡ ምስለ ፡ ላህቡ ፡ ያየብሶ ፡ ለሣዕር ፡

ፀሐይ ፡ ከዋዕዩ ፡ ጋራ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ አገ ዳውን ፡ እንዲያደርቀው ፡

ወፍሬሁኒ ፡ ይወድቅ ፡

ፍሬውም ፡ እንዲረግፍ ፡

ወሥነ ፡ ራእዩኒ ፡ ይትሐጎል ።

ልምላሜውም ፡ እንዲጠፋ ፡

ከማሁኬ ፡ ባዕልኒ ፡ በፍናዊሁ ፡ ይጸመሂ ።

ባለጸጋም ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ይጠፋል ፡ ወብፁዕ ፡ ማንሻ ። አንድም ፡ (ለይትመካሕ) ፡ ድሀው ፡ ወንድማችን ፡ ልዕልና ፡ ነፍስን ፡ በማግኘቱ ፡ ደስ ፡ ይበ ለው ፡ (ወባዕልኒ) ፡ ባለጸጋም ፡ ይገዛ ፡ የነ በረ ፡ በመገዛቱ ፡ አይዘን ፡ (ያዝዝ ፡ የነ በረ ፡ በመታዘዙ ፡ አይዘን ፡ ቢል ፡ ይሆ ናል) ፡ ብዕል፡ እንደ፡ ፍሬ ፡ ሣዕር ፡ ያልፋ ልና ፡ ፀሐይ፡ ከዋዕዩ፡ ጋራ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ አገዳውን፡ እንዲያደርቀው ፡ ፍሬውም፡ እ ንዲረግፍ፡ ልምላሜውም፡ እንዲጠፋ ፡ ባለ ጸጋም ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ይጠ ፋልና ፡ የኀልፍ ፡ ላለው ።

፲፪ ፤ ወብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘይትዔገሥ ፡ ለእኪት ።

መከራን ፡ ታግሦ ፡ የሚቀበላት ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

እስመ ፡ ተመኪሮ ፡ ይነሥእ ፡ አክሊለ ፡ ሕይወት ፡ ዘአሰፈዎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእለ ፡ ያፈቅርዎ ።

በመከራው ፡ ከተፈተነ ፡ በኋላ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ለሚወዱት ፡ ተስፋ ፡ ያናገረ ላቸው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ይወርሳ ልና ፡ (ሐተታ) ፡ አክሊል ፡ አላት ፡ ዘው ድ ፡ የብዕለ ፡ ሥጋ ፡ ፍጻሜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይም ፡ የብዕለ ፡ ነፍ ስ ፡ ፍጻሜ ፡ ናትና ፡ ራእ ፡ ፫፡ ፲፱። ፪ ፡ ጢ ሞ ፡ ፬ ፡ ፰።

፲፫ ፤ ወእመ ፡ ቦ ፡ ዘይትሜከር ፡ ኢይበል ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ያሜክረኒ ።

እዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ በኃጢአት ፡ ይፈትናል ፡ ኃጢአት ፡ ያሠራል ፡ ብለ ዋል ፡ ለዚህ ፡ ያመጣል ፡ ኃጢአት ፡ የሚ ሠራ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃ ጢአት ፡ አሠራኝ ፡ በመከራ ፡ ፈተነኝ ፡ አይበል ፡

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢያሜክር ፡ ለእኪት ።

ኋላ ፡ ለመፍረድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኃ ጢአት ፡ አይፈትንም፡ ኃጢአትን ፡ አያሠ ራምና ።

ወውእቱሰ ፡ ኢያሜክር ፡ ወኢመነሂ ።

እሱስ ፡ ማንንም ፡ ማንን ፡ በኃጢአት ፡ አይፈትንም ፡ ኃጢአት ፡ አያሠራም ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ።

፲፬ ፤ አላ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ ይትሜከር ፡ በፍት ወቱ ፡ እንቲአሁ ።

አንዱም ፡ አንዱም ፡ ወዶ ፡ በሥራው ፡ ኃጢአት ፡ ይፈተናል፡ እንጅ ፡ ኃጢአትን፡ ይሠራል ፡ እንጅ ፡

ወይወፅእ ፡ ኀቤሃ ፡ ወይደነግፅ ።

ሊሠርቅም ፡ ሊቀማም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይወ ጣል ፡ ውደቅ ፡ ሌባ ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ ከሳ ንቃው ፡ ከመድረኩ ፡ ወድቆ ፡ ይማታል ። አንድም ፡ (ወእመቦ) ፡ ኃጢአት ፡ ሠርቶ ፡ በመከራ ፡ የሚፈተን ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ (ኢ ይበል)፡ ኃጢአትን ፡ ሳልሠራ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ መከራን ፡ አመጣብኝ ፡ አይበል ። (እስመ ፡ እግዚአብሔር)፡ ሰውን ፡ ለማሳ ዘን ፡ ኃጢአትን ፡ ሳይሠራ ፡ በመከራ ፡ አይፈትንምና ፡ (መከራን፡ አያመጣምና ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ። (ወውእቱሰ) ፡ እ ሱስ ፡ ማንንም ፡ ማንን ፡ ኃጢአት ፡ ሳይሠ ሩ ፡ በመከራ፡ አይፈትንም ፡ (አላ፡ አሐዱ፡ አሐዱ)፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ ኃጢአት ፡ ሠርቶ ፡ በመከራ ፡ ይፈተናል ፡ እንጅ ። (ወይወፅእ) ፡ ሊሰቀልም ፡ ሊቆረጥም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይወጣል ፡ (ወይደነግፅ) ፡

www.ethiopianorthodox.org

ግንዱ ፡ ተተክሎ ፡ ገመዱ ፡ ተፈትሎ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ይደነግጣል ፡ ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፯ ፡ ፳ ።

፲፭ ፤ ወፍትወትሰ ፡ እምከመ ፡ ፀንሰት ፡ ትወልዳ ፡ ለኃጢአት ።

ነቅዓ ፡ ሐልዮ ፡ በቍዐ ፡ ሐልዮ ፡ የተፈጸመች ፡ እንደሆነ ፡ ነቢብን ፡ ታስከትላለች ።

ወኃጢአትኒ ፡ እምከመ ፡ ተፈጸመት ፡ ትወልዳ ፡ ለሞት ።

ነቢብም ፡ በገቢር ፡ የተፈጸመች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሞትን ፡ ታስከትላለች ። (ሐተታ) ፡ ሴት ፡ ከባሏ ፡ ተለይታ ፡ ከሌላ ፡ ወንድ ፡ ተስማምታ ፡ ዘር ፡ ተቀብላ ፡ ትፀንሳለች ፡ ትወልዳለች ፡ በወተት ፡ በፍትፍት ፡ ታሳድጋለች ፡ ኋላም ፡ ሞትን ፡ ታስከትላለች ፡ በዚያ ፡ አምሳል ፡ ተናግሮታል ፡ ከባሏ ፡ ተለይታ ፡ ከሌላ ፡ ወንድ ፡ ተስማምታ ፡ ዘር ፡ እንድትቀበል ፡ እኛም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተለይተን ፡ ከሰይጣን ፡ ተስማምተን ፡ ምክሩን ፡ እንቀበለዋለን ፤ እንድትፀንስ ፡ የሐልዮ ፡ ኃጢአት ፤ እንደ ፡ መውለድ ፡ የነቢብ ፡ ኃጢአት ፡ በወተት ፡ በፍትፍት ፡ እንደ ፡ ማሳደግ ፡ የገቢር ፡ ኃጢአት ፡ ኋላም ፡ ሞትን ፡ እንድታስከትል ፡ ፍዳን ፡ ሞተ ፡ ነፍስን ፡ እናስከትላለንና ፡ ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፳፫ ።

፲፮ ፤ ኢያስሕትክሙ ፡ አኀዊነ ፡ ፍቁራንየ ።

እናንተ ፡ በናንት ፡ የምትዋደዱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትወዱ ። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወዳችሁ ፡ ፍቁራን ፡ ወንድሞቻችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃጢአት ፡ ያሠራል ። አንድም ፡ ኃጢአት ፡ ሳይሠሩ ፡ በመከራ ፡ ይፈትናል ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ አያስቷችሁ ፤

፲፯ ፤ ኵሉ ፡ ሀብት ፡ ሠናይ ፤

አእምሮ ፡ ጠባይዕ ...

ወኵሉ ፡ ፍት ፡ ፍጹም ፡

አሪት ፡

እምላዕሉ ፡ ይእቲ ፡ ትወርድ ፡ እምኀበ ፡ አቡሃ ፡ ለብርሃን ፡

የወልድ ፡ መገኛ ፤ (አባት ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ከሚሆን ፡ ከአብ ፡ ዘንድ ፡ ተሠርታለች ፡

ውእቱ ፡ ዘአልቦ ፡ ተውላጥ ፡ ኀቤሁ ፡

በባሕርዩ ፡ መለወጥ ፡ የሌለበት ፡

ወአልቦ ፡ ምንትኒ ፡ ዘያመሥጥ ፡ እምእዴሁ ።

ከሥልጣኑ ። አንድም ፡ እዱ ፡ መዝራዕቱ ፡ ከሚባል ፡ ከልጁ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሚያመልጥ ፡ የሌለ ፡ ማር ፡ ፫ ፡ ፯ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፭ ፡

፲፰ ፤ እስመ ፡ በፈቃዱ ፡ ወለደነ ፡ በቃለ ፡ ጽድቁ ፡ ከመ ፡ ንኩን ፡ ቀደምተ ፡ ለፍጥረቱ ።

ለፍጥረቱ ፡ ገዦች ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ወዶ ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርአያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ ባለው ፡ በአካላዊ ፡ ቃል ፡ ፈጥሮናልና ፡ (ወልዶናልና ፡ ይላል) ፡ እምኀበ ፡ አቡሃ ፡ ለብርሃን ፡ ትወርድ ፡ ላለው ። አንድም ፡ (ኵሉ ፡ ሀብት) ፡ ልጅነት ፡ (ጥቅ) ፡ ሀብትኬ ፡ ሠናይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ፍት) ፡ ወንጌል ፡ የዕውቀት ፡ መገኛ ፡ ከሚሆን ፡ ከወልድ ፡ ተሰጣለች ፡ (ዘአልቦ) ፡ ተከታይ ፡ ተቀዳሚ ፡ የሌለበት ፡ ከሥልጣኑ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሚያመልጥ ፡ የሌለ ፡ (እስመ ፡ በፈቃዱ) ፡ ዘአምነ ፡ ወዘተጠምቀ ፡ ይድኅን ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ ወዶ ፡ ወልዶናልና ፤ (ትወርድ ፡ ላለው) ፡ ለፍጥረቱ ፡ ጀማሮች ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ወለደነ ፡ ላለው ። (ሐተታ) ፡ መጀመሪያ ፡ ልጅነትን ፡ ያገኙ ፡ ሐዋርያት ፡ ናቸውና ፡ (ከመ ፡ እለ ፡ ቀደሙነ ፡ ተፈጥሮ ፡ ይላል) ፤ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ የምንነሣው ፡

ሠለስቱ ፡ ምእትን ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ስምንቱን ፡ ሽሕ ፡ ስምንቱ ፡ ሽሕ ፡ ሐዋርያትን ፡ ሐዋርያት ፡ አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ወለደነ ፡ በልጅነት ፡ ነው ፡ ወልዶናልና ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ።

፲፱ ፤ ወይእዜኒ ፡ አኃዊነ ፡ ኩኑ ፡

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ጽኑ ፡

ወይኩን ፡ ኵሉ ፡ ብእሲ ፡ እምኔክሙ ፡ ፍጡነ ፡ ለሰሚዕ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከናንተ ፡ ወገን ፡ የወሬን ፡ የሐሜትን ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡ የቸኮለ ።

ወጕንዱየ ፡ ለነቢብ ፡ ወጕንዱየ ፡ ለመዓት ።

ከመናገር ፡ ከቁጣ ፡ የዘገየ ፡ ይሁን ፡ መክ ፡ ፯ ፡ ፲ ።

፳ ፤ እስመ ፡ መዓቱ ፡ ለብእሲ ፡ ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢይገብሮ ፡

ያንዱ ፡ ቁጣ ፡ አንዱን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ሥራ ፡ አያሠራውምና ፡ (ሐተታ) ፡ የወሬን ፡ ነገር ፡ ይዞ ፡ ሳለ ፡ ለምን ፡ እንዲህ ፡ ታወራለህ ፡ ይለዋል ፡ ምነው ፡ ባወራ ፡ ይለዋል ፡ ከጠብ ፡ ይደርሳሉና ፡ የሐሜትንም ፡ ነገር ፡ ይዞ ፡ ሳለ ፡ ለምን ፡ ታማኛለህ ፡ ይለዋል ፡ ምነው ፡ ባማህ ፡ ይለዋል ፡ ከጠብ ፡ ይደርሳሉና ። አንድም ፡ (ወይኩን) ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡ የቸኮለ ፡ ከመናገር ፡ ከቁጣ ፡ የዘገየ ፡ ይሁን ፡ ያንዱ ፡ ቁጣ ፡ አንዱን ፡ አለ ። የመምህራን ፡ ቁጣ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ የደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ቁጣ ፡ መምህራኑን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ሥራ ፡ አያሠራቸውምና ። ሐተታ ፡ የሥስትነትን ፡ ነገር ፡ ይዞ ፡ ሳለ ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ ተፀቃቢ ፡ ሦስት ፡ አማልክት ፡ ዘጠኝ ፡ አካላት ፡ ማለትህ ፡ ነውን ፡ ይለ

ዋል ፡ ምነው ፡ ብል ፡ ከማለት ፡ ይደርሳልና ፡ ያንድነትን ፡ ነገር ፡ ይዞ ፡ ሳለ ፡ እንደ ፡ ሰባልዮስ ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ ማለትህ ፡ ነውን ፡ ይለዋል ፡ ምነው ፡ ብል ፡ ከማለት ፡ ይደርሳልና ። አንድም ፡ (ኵሉ ፡ ብእሲ) ሰው ፡ ሁሉ ፡ የጦርን ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡ የቸኮለ ፡ ከመናገር ፡ ከቁጣ ፡ የዘገየ ፡ ይሁን ፤ ያንዱ ፡ ቁጣ ፡ አንዱን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ሥራ ፡ አያሠራውምና ፡ (ታሪክ) ፡ እንደ ፡ ክልኤቱ ፡ አኀው ፡ አንዱ ፡ ሕፃን ፡ መናኒ ፤ ነው ፤ አንዱ ፡ ዝጉሐዊ ፡ ባሕታዊ ፡ ጸዋሚ ፡ ተሐራሚ ፡ ነው ፡ ሁሉም ፡ በባጠገብ ፡ ዘግተዋል ፤ በዚያ ፡ ሕፃን ፡ መናኒ ፡ ጦር ፡ ተነሣበት ፤ ሄዶ ፡ አባቴ ፡ ጦር ፡ ተነሣብኝ ፡ አለው ፡ አንተ ፡ ሕርቱም ፡ የእንጦስን ፡ የመቃርስን ፡ ቆብ ፡ ይዘህን ፡ በል ፡ እኮን ፡ ከባትህ ፡ ተመለስ ፡ አለው ፡ ተመልሶ ፡ ሄደ ፡ ሰንብቶ ፡ ተቀሰቀሰበት ፤ ሁለተኛ ፡ ሄዶ ፡ አባቴ ፡ ጦር ፡ ተቀሰቀሰብኝ ፡ ልሂድ ፡ ዓለሙን ፡ መስዬ ፡ እኖራለሁ ፡ አለው ፡ አንተ ፡ ሕርቱም ፡ ተው ፡ አላልሁህም ፡ በልኮ ፡ ከባትህ ፡ ተመለስ ፡ አለው ፡ ተመልሶ ፡ ሄደ ፡ ሰንብቶ ፡ ተቀሰቀሰበት ፡ ከአባ ፡ እገሌ ፡ ዘንድም ፡ ብሄድ ፡ ከቁጣ ፡ በቀር ፡ ያገኘሁት ፡ የለም ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህስ ፡ ዓለሙን ፡ መስዬ ፡ እኖራለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲሄድ ፡ አባ ፡ መቃርዮስ ፡ በጸጋ ፡ ተገልጾለት ፡ ከመንገድ ፡ ቆይቶ ፡ ወዴት ፡ ትሄዳለህ ፡ አለው ፡ ጦር ፡ ተነሥቶብኝ ፡ ዓለሙን ፡ መስዬ ፡ እኖራለሁ ፡ ብየ ፡ እሄዳለሁ ፡ ከአባ ፡ እገሌ ፡ ዘንድም ፡ ብሄድ ፡ ከቁጣ ፡ በቀር ፡ ያገኘሁት ፡ የለም ፡ አለው ፤ ቆይ ፡ ብሎ ፡ ይጸልይ ፡ ጀመረ ፡ የእሱ ፡ ጦር ፡ በዚያ ፡ መነኰሴ ፡ እንዲመለስ ፡ ያንድ ፡ ቀፎ ፡ ንብ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ቀፎ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንዲገለበጥ ፡ ያንድ ፡ ማድጋ ፡ ውኃ፡ ወደ አንድ ፡ ማድጋ ፡ እንዲገባ ፡ የዚያ ፡ ሕፃን ፡ መናኒ ፡ ጦር ፡ በዚያ ፡ ባሕታዊ ፡ ተመል ሶበት ፡ ልዋል ፡ ልደር ፡ ሳይል ፡ መቋሚ ያውን ፡ ይዞ ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ እየበረረ ፡ ሲሄድ ፡ ልብሱን ፡ ያዘው ፡ ተናዶ፡ ተወኝ፡ ተወኝ ፡ አለው ፡ ሄት ፡ አለ ፤ ትእግሥቱ ፡ ከናንተ ፡ ይልቅ ፡ ለኔ ፡ ሰማንያ ፡ ዘመን ፡ ሁኖኛል ፤ ጦር ፡ አልጠፋልኝም ፡ ከሁላ ችንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ጦሩን ፡ ያጥፋ ልን ፡ ብሎ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ሰጥቷ ቸው ፡ ጦር ፡ ጠፍቶላቸው ፡ ከዬባታቸው፡ ተመልሰዋል። አንድም፡ (ወይኩን፡ ኩሉ፡ ብእሲ) ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የማኅበሩን ፡ ነገር ፡ (የገዳሙንም ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ለመ ስማት ፡ የቸኮለ ፡ ከመናገር ፡ ከቁጣ ፡ የዘ ገየ ፡ ይሁን ፡ ያንዱ ፡ ቁጣ ፡ አንዱን ፡ እግ ዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ሥራ ፡ አያሠ ራውምና ፡ የአበ ፡ ማኅበሩ ፡ ቁጣ ፡ ማኅ በሩን ፡ የማኅበሩ ፡ ቁጣ ፡ አበ ፡ ማኅበሩን ፡ ታሪክ፡ እንደ ፡ አባ፡ መቃርዮስ፡ አባ፡ ታዎ ሚጦስ ፡ ሴት፡ ለምዶ፡ በዓቱን፡ ጥሎ ፡ እየ ወጣ ፡ ያድር ፡ ጀመር ፡ እየወጣ ፡ ያድርል ሃል፡ ብለው፡ ነገሩት፤ ተዉ፡ እኮን፡ ደጉን ፡ ልጄን ፡ አላቸው ፡ ከበዓቱ ፡እያመጣ ፡ ያሳ ድራት ፡ ጀመር ፡ እረ ፡ ከበዓቱ ፡ ያሳድ ራት ፡ ጀመር ፡ አሉት ፡ ተዉ ፡ አላልኋ ችሁምን ፡ አላቸው ፡ አንድ ፡ ቀንም ፡ ይል ማ ፤ ይስማ ፡ ብላ ፡ ቀና ፡ ለቀን ፡ ዘው ፡ ብላ ፡ ገባች ፡ ዛሬስ ፡ ይልማ ፡ ይስማ ፡ ብላ፡ ቀና ፡ ለቀን ፡ ዘው ፡ ብላ ፡ ገባችልህ ፡ አሉ ት ፡ እንግዲህማ ፡ እሱ ፡ ቢፈቅድለት ፡ ነው ፡ ሲሉኝ ፡ አይደለም ፡ ተነሡ ፡ እን ሂድ ፡ አላቸው ፡ አኀዛውን ፡ አስይዞ ፡ ማኅ በሩን ፡ አስከትሎ ፡ ሄዶ ፡ ከአጠገቡ ፡ ሲደርስ፡ ድምፅ፡ እያሰማ ፡ ገባ ፡ ደንግጦ ፡ ቅርጫት ፡ አንሥቶ ፡ ደፋባት ፡ ከዚያ ፡ እንዳለች ፡ ዐውቆ ፡ አኀዛውን ፡ ከዚያ ፡ ላይ)፡ አንጥፉልኝ ፡ አላቸው ፡ ከዚያ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ በሉ ፡ ፈልጉ ፡ አላቸው ፡ ቢገቡ ፡ ቢወጡ ፡ አጠዋታል ፡ እኔማ ፡ አላልኋችሁምን፡አላቸው፡አሁንም፡ከእሱ፡ ጋራ ፡ የምንጋገረው ፡ ነገር ፡ አለኝና ፡ ቆዩ፡ አላቸው ፡ ልጄ ፡ እንደምን ፡ ነህ ፡ ጦር ፡ ጠፍቶልሃልን ፡ አለው ፡ አባቴ ፡ በአንተ፡ ኀዘን ፡ ጠፍቶልኛል ፡ አለው ፡ ወልድየ ፡ ፍታሕ ፡ በርእስከ ፡ እምቅድመ ፡ ይፍ ታሕ ፡ ብከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪከ ፡ አለው ፡ አባቴ ፡ ብፈራህ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ከሱ ፡ ከተቀመጥህበት ፡ ውስጥ ፡ አለች ልህ ፡ አለው ፡ ወዮ ፡ ብሎ ፡ አስወጥቶ ፡ ለምን ፡ እንዲህ ፡ አደረግሽ ፡ አላት ፡ እሳ ቸው ፡ ቢያመጡኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ሳድርግ ፡ አለችው፡ አንተስ፡ ለምን ፡ እንዲህ፡ አደረግህ፡ አለው፡ ምን፡ ሳድርግ ፡ እህል ፡ በቀመስሁ ፡ ጊዜ ፡ ጦር ፡ ይጸናብ ኛል፤አለው ፡ ውለህ ፡ ተመገብ ፡ ምግብ ፡ አታሻሽል፡ ወንጌለ፡ ዮሐንስ፡ ድገም፡ ብሎ ት ፡ ወጥቶ ፡ ሲሄድ ፡ ዕፀው ፡ አዕባን ፡ እዬ ተከተሉ ፡ መቃርዮስ ፡ ኮነ ፡ አምላከ ፡ በ ዲበ ፡ ምድር ፡ መቃርዮስ ፡ ኮነ ፡ ከሃሌ ፡ ከመ፡ አምላኩ፡ ብለው፡ አመስግነውታል። አንድም ፡ (ኵሉ ፡ ብእሲ) ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የንስሓን ፡ ነገር፡ ለመስማት፡ የቸኮለ፡ ከመ ናገር ፡ ከቁጣ ፡ የዘገየ ፡ ይሁን ፤ የመምህረ፡ ንስሓው ፡ ቁጣ ፡ ተነሳሒውን ፡ የተነሣ ሒው ፡ ቁጣ ፡ መምህረ ፡ ንስሓውን ፡ እግ ዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ሥራ ፡ አያሠ ራውምና ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ ሠር ቻለሁ ፡ ይለዋል ፡ እንዲህ ፡ አደረግህን ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተመልሶ ፡ ሁለተኛ ፡ አይደርስበትምና ፡ ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፳፮ ።

፳፩ ፤ ወይእዜኒ ፡ ኅድግዋ ፡ ለኵሉ ፡ ርስሐት ፡ ወለ ኵሉ ፡ እኪት ፡

አሁንም ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ የእፍአ ፡ የው ስጥ ፡ ኃጢአትን ፡ አፍአዊ ፡ ውሳጣዊ ፡ ክፋትን ፡ ከናንት ፡ አርቋት ፡

ወበየዋሃት ፡ ተቀበልዎ ፡ ለቃል ፡ ዘተዘርዐ ፡ ውስተ ፡ ልብክሙ ፤

ተቀበልዎ ፡ ውስተ ፡ ልብክሙ ፡ ዘተዘ ርዐ ፡ ውስተ ፡ ልብክሙ ፡ (ግጥ) ፡ ለልቡ ናችሁ ፡ የተነገረውን ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔ ር ፡ ወንጌልን ፡ በልቡናችሁ ፡ ተቀበሉት፡

ዘይክል ፡ አድኅኖታ ፡ ለነፍስክሙ ፡

ነፍሳችሁን ፡ ማዳን ፡ የሚቻለው ፡ ብሎ ፡ ለወንጌል ፡ ቀጠለ ፡ ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፱ ። ቆላ፡ ፫ ፡ ፳ ።

፳፪ ፤ ወኩኑ ፡ ገባርያኒሃ ፡ ለሕግ ፡

ፈጻምያን ፡ ሕግ ፡ ሁኑ ፡

ወአኮ ፡ ለአፅምኦ ፡ ባሕቲቱ ፡

ለመስማት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡

ሐልይዎ ፡ እስኩ ፡ ለሊክሙ ።

እስኪ ፡ እናንት ፡ ፍረዱት ፡ ማቴ ፡ ፯፡ ፳፩። ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ።

፳፫ ፤ እመ ፡ ቦ ፡ ዘያፀምኦ ፡ ለቃል ፡ ወኢይገብሮ ፡

ሕጉን ፡ ሰምቶ ፡ የማይፈጽመው ፡

ይመስል ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘይሬኢ ፡ ፍጥረተ ፡ ገጹ ፡ በመጽሔት ።

ሰውነትን ፡ ለመረዳት ፡ ፊቱን ፡ በመስታ ዋት ፡ የሚያየውን ፡ ሰው ፡ ይመስላል ፡ ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፵፱ ።

፳፬ ፤ ወጠይቆ ፡ ርእሶ ፡ ኀለፈ ፡ ወረስዐ ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ውእቱ ።

ጠይቆ ፡ ርእሱ ፡ ርእሶም ፡ ይላል ፡ በዐ ይኑ ፡ ጉድፍ ፡ በጥርሱ ፡ እድፍ ፡ አይቶ ፡ ጉድፉን ፡ ሳንሣው ፡ እድፉን ፡ ልክላው ፡ ሳይል፡የቀረውን፡ ሰነፍ፡ ሰው፡ ይመስላል ፡ እንደ ፡ ማየት ፡ መማር ፡ ጉድፉን ፡ ሳን ሣው ፡ እድፉን ፡ ልክላው ፡ እንዳለማለት ፡ ሥራውን ፡ አለመሥራት ። አንድም ፡ ፊ ቱን ፡ ልይ ፡ ብሎ ፡ መስታዋት ፡ አውጥቶ ፡ ሳያይ ፡ የቀረውን ፡ ሰው ፡ ይመስላል ፡ (አይቶ ፡ ሲያጥፈው፡ የሚዘነጋውን፡ ቢል ፡ ይቀናል) ፡ልይ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ እማራ ለሁ ፡ ማለት ፡ ሳያይ ፡ እንደ ፡ መቅረት ፡ አለመማር ።

፳፭ ፤ ወዘሰ ፡ ሐወጸ ፡ ውስተ ፡ ሕግ ፡ ፍጹም ፡ ዘየ ግዕዝ ።

ግዕዛን ፡ ነፍስን፡ የሚያሰጥ፡ ፍጹም፡ ሕግ ፡ ወንጌልን ፡ የሚመለከት ፡ ግን ፡ ውስተ ፡ ግዕዝ ፡ ነው ፡ (ጥቅ) ፡ አንብብ ፡ ውስተ ፡ ወንጌል ፡ እንዲል ፡

ወተዐገሠ ።

መከራውን ፡ ታግሦ ፡ የሚቀበል ፡

ኢኮነ ፡ ራስዐ ፡ ዘሰምዐ ።

የተማረውን ፡ የሰማውን ፡ የዘነጋ ፡ አይ ደለም ፡ ረሲዐ ፡ ረሳዔም ፡ ይላል ፡

አላ ፡ ገባሬ ፡ ሕግ ፡ ውእቱ ።

ፈጻሚ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡

ብፁዕ ፡ ዝንቱ ፡ በምግባሩ ።

ወብፁዕ ፡ ማንሻ ። አንድም ፡ ግዕዛን ፡ ነ ፍስ ፡ ወንጌልን ፡ የሚመለከት ፡ መከራው ንም ፡ ታግሦ ፡ የሚቀበል ፡ የሰማውንም ፡ የዘነጋ ፡ ያይደለ ፡ ፈጻሚ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ እ ንጅ ፡ የሰማውንም ፡ የዘነጋ ፡ ያይደለ ፡ በ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ።

፳፮ ፤ ወእመ ፡ ቦ ፡ ዘይመስሎ ፡ ከመ ፡ ዘይትሔረም፡ ለእግዚአብሔር ፡

ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ትሕርምት ፡ የያ ዘ ፡ የሚመስለው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኢ.ያለጉሞ ፡ ለልሳኑ ።

አንደበቱን ፡ ከሐሜት ፡ ከፅዕለት ፡ ከቧ ልት ፡ ያልከለከለ ፡

ወአስሐቶ ፡ ለልቡ ።

ልቡናውን ፡ በሐሜት ፡ በፅዕለት ፡ በቧ ልት ፡ ያሳተ ፡

ለዘከማሁ ፡ ከንቱ ፡ ሐርመቱ ።

ለንዲህ ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ ሕርመቱ ፡ ከንቱ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘለትን፡ ምግብ፡ ትቶ ፡ የሰይጣንን ፡ ምግብ ፡ ከተመገበ ፡ መገ፤ ፡ ፴፩ ፡ ፲፩ ።

፳፯ ፤ ወሐርመትሰ ፡ ንጽሕት ፡ እንተ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ።

ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዘንድ ፡ የተገኘ ች ፡ የምትገባ ፡ ሕርመትስ ፡ ይህች ፡ ናት ፡

ከመ ፡ ትፅቀቡ ፡ እጓለ ፡ ማውታ ፡ ወእቤራተ ፡ በተፅ ናሰሙ ።

እናት፡ አባት፡ የሞቱበትን፡ ረድ፡ልጅ፡ የሌ ላቸውን ፡ በችግራቸው ፡ ጊዜ ፡ በነገር ፡ በጉልበት ፡ ትረዷቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡

ወትዕቀቡ፡ርእሰክሙ፡ እምዓለም፡ዘእንበለ፡ሐብቃቁ ።

ሳትጣሉ ፡ ከፈቃደ ፡ ሰይጣን ፡ ሰውነታች ሁን ፡ ጠብቃችሁ ። እግዚአብሔርን ፡ ለ ማገልገልም ። አንድም ፡ (ወእመሰ ፡ ቦ) ፡ ጾም ፡ የሚጾም ፡ የሚመስለው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ አለ ፡ የሚጾም ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ (ወኢ.ያለጉሞ)፡ አንደበቱን፡ ልጓዛ፡ ላብዛ ፡ ከማለት ፡ ያልከለከለ ፡ (ለዘከመዝ) ፡ ለን ዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው፡ ጾሙ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ጾም ፡ እየዋለ ፡ በምሳ ፡ ከበር ፡ ይባላል ፡ (ወሐርመትሰ) ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታዘዘች፡ የምትገባ፡ ጾምስ፡ ይህች፡ ናት ፡ (ከመ ፡ ትዕቀቡ) ፡ እናት ፡ አባት ፡ የሞቱ በትን ፡ ረድ ፡ ልጅ ፡ የሌላቸውን ፡ በችግ ራቸው ፡ ጊዜ፡ በክብት ፡ ትረዱ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ (ወትዕቀቡ) ፡ ሳትሳሱ ፡ ሰውነታች ሁን ፡ ከፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ከልክላችሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፤ አኀዊነ ፡ ኢ.ትኩን ፡ ለገጽ ፡ ሰብእ ፡ ሃይማኖት ክሙ ፡ እንተ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢ.የሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ወንድሞቻችን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የምትሆን ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ ለሰው ፡ ይምሰል ፡ በአፍኣ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመባል ፡ ብቻ ፡ አትሁን ፡

ዘሎቱ። ስብሐት ።

ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ሎቱ ፡ ስብ ሐት ፡ የያዕቆብ ፡ ቃል፡ ነው፡ ይህንንም ፡ ይዘው ፡ ሊ.ቃውንት ፡ ሎቱ፡ ኀይል ፡ ሎቱ፡ ዕበይ ፡ ሎቱ ፡ ዕዘዝ ፡ ሎቱ ፡ ፅንዕ ፡ እያሉ፡ አምልተው ፡ አስፍተው ፡ ተናግረውታል ፡ (በከመ ፡ ይቤ ፡ ያዕቆብ ፡ እያሉ ፡ ወሰደው ታልም ፡ ይላሉ) ።

፪ ፤ ከመ ፡ እመ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ ማኅበርክሙ ፡ ብእሲ ፡ ዘሕልቀተ ፡ ወርቅ ።

ከዚህም ፡ ድሀና ፡ ባለጸጋ ፡ ካንድ ፡ ማኅ በር ፡ ቤት ፡ ገብተዋል ፡ ባለጸጋውን ፡ አክብረው ፡ ድሀውን ፡ አዋርደው ፡ አይተ ውታል ፤ ለዚህ ፡ ያመጣል ፡ የወርቅ ፡ ቀለ በት ፡ ያደረገ ፡

ወዘአልባስ ፡ ንጹሕ ፡

ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ የለበሰ ፡ ከማኅበራ ችሁ ፡ ቢገባ ፡

ወቦአ ፡ ነዳይ ፡ በአልባስ ፡ ርሱሕ ።

ጨርቅ ፡ ለባሽ ፡ ድሀ ፡ ከማኅበራችሁ ፡ ቢገባ ። (ሐተታ) ፡ ወርቅ ፡ ቀለበት ፡ አድ ርጎ ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ ለብሶ ፡ የሚ ገባ ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ፡ ወርቅ ፡ ግምጃ ፡ ትእምርተ ፡ ብዕል ፡ ነው ።

፫ ፤ ወትኔጽርዎ ፡ ለዘይለብስ ፡ ንጹሐ ።

ባለ ፡ ጸጋውን ፡ አክብራችሁ ፡ ብታዩት ፡

ወትብልዎ ፡ አንተሰ ፡ ንበር ፡ ዝየ ፡ ውስተ ፡ ምሥ ናይ ፡

አንተስ ፡ ምንጣፍ ፡ መጠጊያ ፡ ካለበት ፡ ጽዋ ፡ ከሚጀመርበት ፡ ተቀመጥ ፡ ብት ሉት ፡

ወለነዳይሰ ፡ ትብልዎ ፡ ቁም ፡ ከሓከ ፡ አንተሰ ፡

ድሀውን ፡ ግን ፡ አንተስ ፡ ወዲያ ፡ ወግድ ፡ ብትሉት ፡

ወእመ ፡ አኮ ፡ ንበር ፡ ታሕተ ፡ መከየደ ፡ እገሪነ ።

ያውም ፡ ባይሆን ፡ መጠጥ ፡ ከወረደበት ፡ ጽዋ፡ ከተደረደረበት፡ እሳት ፡ ከነደደበት፡ እግራችንን፡ እያሸህ፡ ተቀመጥ፡ ብትሉት ።

፬ ፤ አኮኑ ፡ እንከ ፡ አድሎክሙ ፡ ለሊክሙ ፡

ለራሳችሁ ፡ ማድላታችሁ ፡ አይደለምን ፡

ወኮንክሙ ፡ መደልዋነ ፡ ለሕሊና ፡ እኩይ ።

ለግብዝ ፡ ሕሊናስ ፡ ምቹ ፡ መሆናችሁ ፡ አይደለምን ። አንድም ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ፡ እንድትሉት ፡ መጠን ፡ ለራሳችሁ ፡ ማድ ላታችሁ ፡ ነውና ፡ ለግብዝ ፡ ሕሊናም ፡ ምቹ ፡ መሆናችሁ ፡ ነውና ፡ ኢ.ትኩን ፡ ለገጸ ፡ ሰብእ ፡ ላለው ። አንድም ፡ የባለ ፡ ጸጋ ፡ ልጅና ፡ የድሀ ፡ ልጅ ፡ ካንድ ፡ ትም ህርት ፡ ቤት ፡ ገብተዋል ፡ የባለ ፡ ጸጋውን፡ ልጅ ፡ አክብረው ፡ አይተውታል ፤ የድሀ ውን ፡ ልጅ ፡ ንቀው ፡ አቃለው ፡ (አዋር ደው ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ አይተው ታል ፡ ለዚህ ፡ ያመጣል ፡ (ከመ ፡ እመ ፡ ቦአ) ፡ የባለ ፡ ጸጋ ፡ ልጅ ፡ ከትምህርት ፡ ቤታችሁ ፡ ቢገባ ፡ (ወቦአ ፡ ነዳይ) ፡ የድሀ፡ ልጅ ፡ ከትምህርት ፡ ቤታችሁ ፡ ቢገባ ፡ (ወትኔጽርዎ) ፡ የባለ ፡ ጸጋውን ፡ ልጅ ፡ አክብራችሁ ፡ ብታዩት ፡ አንተስ ፡ እኛ ፡ የበላነውን ፡ በልተህ ፡ እኛ ፡ የጠጣነውን ፡ ጠጥተህ ፡ እኛ ፡ የለበስነውን ፡ ለብሰህ ፡ ተማር ፡ ብትሉት ፡ (ወለነዳይሰ) ፡ የድሀ ውን ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ አንተስ ፡ ወዲያ ፡ ወ ግድ ፡ ብትሉት ፡ ያውም ፡ ባይሆን ፡ ዕን ጨት ፡ እየሰበርህ ፡ ውኃ ፡ እየቀዳህ ፡ እግ ራችንን ፡ እያጠብህ ፡ አገልግለን ፡ ብት ሉት ፡ ለራሳችሁ ፡ ማድላታችሁ ፡ አይደ ለምን ፡ ለግብዝ ፡ ሕሊናስ ፡ ምቹ ፡ መሆ ናችሁ፡ አይደለምን ። አንድም ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ እንድትሉ ፡ መጠን ፡ ለራሳችሁ፡ ማድላታችሁ ፡ ነውና፡ ለግብዝ፡ ሕሊናም ፡ ምቹ ፡ መሆናችሁ ፡ ነውና ፡ ኢ.ትኩን ፡ ለ ገጸ ፡ ሰብእ ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ ላለው ።

፭ ፤ ስምዑ ፡ አኀዊነ ፡ ፍቁራን ፡

ፍቁራን ፡ ወንድሞቻችን ፡ ስሙ ፡

አኮኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀረዮሙ ፡ ለነዳይነ ፡ ዝ ፡ ዓለም ፡

የዚህን ፡ ዓለም ፡ ድሆች ፡ እግዚአብሔር ፡ ለወንድምነት፡ ለምክንያት፡ የመረጣቸው፡ አይደለምን ፡ መርጠዋቸዋልና ፡ ስምዑ ፡ ዕወቁ ።

ወአብዕልትሰ ፡ ከመ ፡ በሃይማኖቶሙ ፡ ይወርስዋ ፡ ለመንግሥት፡ እንተ፡ አሰፈዎሙ፡ ለእሉ፡ ያፈቅርዎ ።

ነዳያንን ፡ ብቻ ፡ ባለጸጎችንሳ ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለ ጸጎችም ፡ ለሚወዱት ፡ ሰዎች፡ ተስፋ ፡ ያናገረላቸው፡ መንግሥት፡ ሰማይን ፡ በሃይማኖታቸው ፡ እንዲወር ሷት ፡ ተጽፍዋል ። አንድም ፡ ባለጸጎችስ ፡ በሉኝ ፡ ነዳያን ፡ በሃይማኖታቸው ፡ መን ግሥት፡ ሰማይን፡ እንዲወርሷት፡ መጠን ። አንድም ፡ (አኮኑ ፡ እግዚአብሔር) ፡ የዚ

www.ethiopianorthodox.org

ሀን ፡ ዓለም ፡ ነዳያን ፡ ልብደ ፡ ሠሪ ፡ ዓማ፡ እስጋሪ፡ የነበሩ፡ ሐዋርያትን ፡ ለወንድም ነት፡ ለአብነት፡የመረጣቸው፡ አይደለምን፡ ነዳያንን ፡ ብቻ ፡ ባለጸጎችሳ ፡ ትሉኝ ፡ እን ደ ፡ ሆነ ፡ ባለጸጎችም ፡ እለ ፡ ማቴዎስ ፡ እለ ፡ ዘኪዎስ ፡ በሃይማኖታቸው ፡ መንግ ሥተ ፡ ሰማይን ፡ እንዲወርሷት ፡ ተጽ ፍዋል ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፯ ። ዘፀአ ፡ ፳፯ ።

፮ ፤ ወአንትሙሰ ፡ አስተሐቀርክምዎሙ ፡ ለነዳያን፤

እናንተ ፡ ግን ፡ ነዳያንን ፡ ናቃችኋቸው ፡ አቃለላችኋቸው ፡

አኮኑ ፡ አብዕልት ፡ እሉ፡ ይትዔገሉክሙ፡ ወይስሕቡ ክሙ ፡ ውስተ ፡ ተስናናት ፡ ወአዕዋዳት ።

ባለጸጎችማ ፡ እንዳትንቋቸው ፡ እንዳታቃ ልሏቸው ፡ አዳርሱን ፡ እያሉ ፡ ወደ ፡ አደ ባባይ ፡ ወደ ፡ ፀብ ፡ ወደ ፡ ክርክር ፡ የሚወ ስዷችሁ፡ የሚያደርሷችሁ ፡ አይደለምን ።

፯ ፤ ወእሙንቱ ፡ ይፀርፉ ፡ ላዕለ ፡ ስሙ ፡ ዐቢይ ፡ ዘተሰምየ ፡ ላዕሌክሙ ።

ነዳያን ፡ ግን ፡ የተጠራችሁበት ፡ ስሙን ፡ ይነቅፉሉ ፡ እንጅ ፡ የሚሏችሁ ፡ የለም ፡ ክርስቲያን ፡ ሲባሉ ፡ እንዲህ ፡ መሆን ፡ እያሉ ።

፰ ፤ ወእመሰ ፡ ትፌጽሙ ፡ ሕገ ፡

ሁሉንስ ፡ አስተካክላችሁ ፡ ብትወዱ ፡ ፈጻ ምያን ፡ ሕግ ፡ ትባላላችሁ ፡

በከመ ፡ ይብል ፡ መጽሐፍ ፡ አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ከመ ፡ ነፍስከ ።

መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ከመ ፡ ነፍስከ ፡ ብሎ ፡

ወሠናየ ፡ ትገብሩ ፡

ማንሻ ። አንድም፡ ወእመሰ ፡ ትፌጽሙ) ፡ ሕጉንስ ፡ ብትፈጽሙ ፡ እለ ፡ ሁሉን ፡ አ ስተካክላችሁ፡ ብትወዱ ፡ መጽሐፍ ፡ አፍ ቅር፡ ቢጸከ ፡ ከመ ፡ ነፍስከ ፡ ብሎ ፡ እንደ፡ ተናገረ፡ (ሠናየ፡ ትገብሩ)፡ ዋጋችሁን፡ ታገ ኛላችሁ ፡ ማር ፡ ፲፪፡ ፴፩። ዘሌዋ፡ ፲፱፡ ፲፰ ፡

፱ ፤ ወእመሰ ፡ ገጸ ፡ ትነሥኡ ፡ ኃጢአተ ፡ ትገብሩ፡

ፊት ፡ አይታችሁ ፡ ብታደሉ ፡ ግን ፡ ፍዳ ችሁን ፡ ትቀበላላችሁ ።

ወይዛለፈክሙ ፡ ሕግ ፡ ከመ ፡ ከሐዲ ።

ከሐድያን ፡ እንደ ፡ መሆናችሁ ፡ ከሐዲን ፡ እንዲዘልፉት ። አንድም ፡ እንደ ፡ ተከራ ካሪ ፡ ሕግ ፡ ይዘልፋችኋል ፡ ዘዳግ ፡ ፩ ፡ ፲፯ና ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ።

፲ ፤ ወዘሰ ፡ ይገብሮ ፡ ለኵሉ ፡ ሕግ ፡ ወይስሕት ፡ በአሐቲ ፡

ሕጉን ፡ ሁሉ ፡ የሚፈጽም ፡ አንዲቱን ፡ የ ሚያፈርስ ፡

ኮነ ፡ መአብሰ ፡ በኵሉ ።

ሕጉን ፡ ሁሉ ፡ አፈረሰ ። (ሐተታ) ፡ መለ ያየት፡ከጀመረ፡ ሁሉን፡ እስከ ፡ ማፍረስ ፡ ይደርሳልና ፡ ዳዊት ፡ ኢትፍቱን ፡ ቢያ ፈርስ ፡ ኢትዘሙና ፡ ኢትቅትል ፡ እን ዳልቆሙለት ፡ አሥር ፡ ደጅ ፡ አፍ ፡ ያለ ው ፡ ቤት ፡ ዘጠኙ ፡ ሁሉ ፡ ተዘግቶ ፡ አን ዱ ፡ ክፍት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጠላት ፡ በዚያ ፡ ገብቶ ፡ የባለ ፡ ቤቱን ፡ ቾብቾቦ ውን ፡ ቈርጦ ፡ ገንዘቡን ፡ ዘርፎ ፡ ሲሄድ ፡ የዘጠኙ ፡ መዘጋት ፡ እንዳያድነው ፡ ዘጠ ኙን ፡ መጠበቁ ፡ አንዱን ፡ በማፍረሱ ፡ የሚመጣበትን፡ ፍዳ፡ አያስቀርለትም፡ እን ደዚሁም ፡ ላንዱ ፡ መስጠቱ ፡ ላንዱ ፡ በመ ንሣቱ ፡ የመጣበትን ፡ ፍዳ ፡ አያስቀርለ ትምና ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ።

፲፩ ፤ እስመ ፡ ዘይቤ ፡ ኢትሑር ፡ ኀበ ፡ ብእሲተ ፡ ብእሲ ፡

ከጉልማሳ ፡ ምሽት ፡ አትሂድ ፡ ያለ ፡ መጽ ሐፍ ፡ ያለ ፡ ጌታ ፡ ያለ ፡ ሙሴ ፡ ያለ ፡ አ ዳም ፡

ይቤ ፡ ኢትቅትል ፡ ነፍሰ ፡

ነፍስ ፡ አትግደል ፡ ብሏልና ፡

ወእመሰ ፡ ኢተሐውር ፡ ኀበ ፡ ብእሲተ ፡ ብእሲ ፡

ከጉልማሳ ፡ ምሽት ፡ (ተሐውር) ፡ አለመ ሄድን ፡ ብትሄድ ፡

ወባሕቱ ፡ ትቀትል ፡ ነፍሰ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ነፍስ ፡ ብትገል ፡

ኮንከ ፡ ውፁአ ፡ እምሕግ ።

ከሕግ ፡ የወጣህ ፡ ሆንህ ። (ሐተታ) ፡ ከጉ ልማሳ ፡ ምሽት ፡ አለመሄዱ ፡ ነፍስ ፡ በመ ግደሉ ፡ የመጣበትን ፡ ፍዳ ፡ አያስቀርለ ትም ፡ እንደዚሁም ፡ ላንዱ ፡ መስጠቱ ፡ ላንዱ ፡ በመንሣቱ ፡ የሚመጣበትን ፡ ፍዳ፡ አያስቀርለትምና ። አንድም ፡ ከጉልማሳ ፡ ምሽት ፡ አትሂድ ፡ ያለ ፡ መጽሐፍ ፡ ያለ ፡ ጌታ ፡ ያለ ፡ አዳም ፡ ነፍስ ፡ እንጅ ፡ እን ዳትገል ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ ኢተሐውር ፡ ከጉልማሳ ፡ ምሽት ፡ አለመሄድን ፡ ባት ሄድ ፡ (ብትሄድ ፡ ማለት ፡ ነው) ፡ ነፍስ ፡ እንጅ ፡ ትገላለህ ፡ እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ከ ሕግ ፡ የወጣህ ፡ ሆንህ ፡ (ሐተታ) ፡ ቢገል ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ተብሎ ፡ ይፈረድበታል ፤ ቢሞትም ፡ ወኮኑ ፡ ቀታልያነ ፡ ርኢሰሙ ፡ ከተባሉት ፡ ይቈጠራልና ፡ ዘፀአ ፡ ፳ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

፲፪ ፤ ከመ ፡ ዝ ፡ ንግሩ ፡ ወከመ ፡ ዝ ፡ ግበሩ ፡

እንዲህ ፡ ብላችሁ ፡ ንገሩ ፡ እንዲህ ፡ አድ ርጋችሁ ፡ ሥሩ ። አንድም ፡ እንዲህ ፡ አድርጋችሁ ፡ ሥሩ ፡ ብላችሁ ፡ እንዲህ ፡ ብላችሁ ፡ አስተምሩ ፡

ከመ ፡ ዘበሕገ ፡ ግዕዛን ፡ ሀለውክሙ ፡ ትትኴነኑ ፡

በሕገ ፡ ግዕዛን ፡ በወንጌል ፡ ይፈረድባ ችሁ ፡ ዘንድ ፡ እንዳላችሁ ፡ መጠን ። አን ድም ፡ ዘበሕገ ፡ ግዕዛን ፡ ሀለውክሙ ፡ በሕገ ፡ ግዕዛን ፡ በወንጌል ፡ ያላችሁ ፡ እና ንተ ፡ እንዲፈረድባችሁ፡ አውቃችሁ ፡ ሮም፡ ፩ ፡ ፳፭ ።

፲፫ ፤ እስመ ፡ በደይንስ ፡ አልቦ ፡ ምሒር ፡ ለዘኢገ ብረ ፡ ምሕረተ ፡

የርኅራኄ ፡ ሥራ ፡ ሳልሠራ ፡ ፍትሐ ፡ ር ቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ በቁርጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ አይ ራሩለትምና ፡

ወይትሜካሕ፡ ባሕቱ ፡ በዕለተ ፡ ደይን ፡ ዘገብረ ፡ ምሕ ረተ ።

የርኅራኄ ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ በቁርጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ እንጅ ። ማቴ፡፭፡ ፯ና፡ ፲፰፡ ፴፡ ፴፩ና፡ ፳፭፡ ፵፭፡ ፵፯፡

፲፬ ፤ ምንት ፡ ይበቍዕ ፡ አኀዊነ ፡

ወንድሞቻችን ፡ ምን ፡ ይረባል ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ፡

ለእመ ፡ ቦ ፡ ዘይብል ፡ ሃይማኖት ፡ ብየ ፡ ወምግባረ ፡ ሠናይ ፡ አልብየ ፡

ሃይማኖት ፡ አለኝ ፡ ምግባር ፡ የለኝም ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ (ምግባርስ ፡ የለ ኝም ፡ አይልም ፡ ብሎ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ አልቦ)፡ ሃይማኖት ፡ ያለው ፡ ምግባር ፡ የሌ ለው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ምን ፡ ይረባዋል ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ፡

ቦኑ ፡ ተክል ፡ ሃይማኖቱ ፡ አድኅኖቶ ።

በውኑ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ብቻ ፡ ሊታድነው ፡ ይቻላታልን፡ ሐተታ፡ ምነው፡ ዘአ፡ ይት ከሃል፡ ለዘየአምን ፡ ይል፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ በዚያም፡ እንጅ፡ ወዝንቱ፡ ዘመድ፡ ኢይወ ፅእ ፡ ዘእንበለ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ያለ በት ፡ ነው ፡ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፳፯ ።

፲፭ ፤ ለእመ ፡ ቦ ፡ እምአኀዊነ ፡ አው ፡ እምአኃቲነ ፡ እለ ፡ ዕሩቃን ፡ እሙንቱ ፡ አው ፡ ኅጡአን ፡ ለሲሳየ ፡ ዕለቶሙ ።

ከወንድሞቻችን ፡ ከእኅቶቻችን ፡ የዕለት ፡

www.ethiopianorthodox.org

እሯት ፡ ያመት ፡ ልብስ ፡ አጥተው ፡ የተ
ቸገሩ ፡ ሰዎች ፡ ቢኖሩ ፡ ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

፲፮ ፤ ወቦ ፡ ዘይቤሎሙ ፡ እምኔክሙ ፡ ሑሩ ፡ በሰላም ፡

ከናንት ፡ ወገን ፡ በደኅና ፡ ሂዱ ፡

ሰሐኑ ፡ ወትጸግቡ ፡

እገሌ ፡ ለጋስ ፡ ነው ፡ አብልቶ ፡ ያጠግ
ባል ፡ አልብሶ ፡ ያሞቃል ፡ ቢላቸው ፡

ወኢወሀብሙ ፡ ዘይፈቅዱ ፡ ለተጽናሶሙ ።

ግዳጃቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ የሚሹትን ፡
ካልሰጣቸው ፡

ምንተ ፡ ይበቍዖሙ ።

ምን ፡ ይረባቸዋል ፡ ምን ፡ ይጠቅማቸዋል ፡
(ሐተታ) ፡ ምነው ፡ ጠቋሚ ፡ ጠቃሚ ፡ እን
ዴት ፡ ቢጠቁማቸው ፡ ቢሉ ፡ ይሰጠናል ፡
ብለው ፡ ሂደዋል ፡ እንጅ ፡ ይጠቁመናል ፡
ብለው ፡ ሂደዋልን ፡ በዚያውስ ላይ ፡
እሱማ ፡ ካልሰጣቸው ፡ ያም ፡ እንደእሱ ፡
ነው ። ይሉት ፡ የለምን ። አንድም ፡ (ወእ
መ ፡ ቦ) ፡ በደኅና ፡ ሂዱ ፡ እግዚአብሔር ፡
አብልቶ ፡ አጠጥቶ ፡ ያጥግባችሁ ፡ አል
ብሶ ፡ ያሙቃችሁ ፡ ቢላቸው ፡ ግዳጃቸው
ን ፡ ለመፈጸም ፡ የሚሹትን ፡ ካልሰጣ
ቸው ፡ ምን ፡ ይረባቸዋል ፡ ምን ፡ ይጠቅ
ማቸዋል ፡ (ሐተታ ፡ ምነው ፡ ቢመርቃ
ቸው ፡ ቢሉ ፡ ይሰጠናል ፡ ብለው ፡ ሂደ
ዋል ፡ እንጅ ፡ ይመርቀናል ፡ ብለው ፡ ሂደ
ዋልን ፡ በዚያውስ ፡ ላይ ፡ እሱ በመር
ኀም ፡ ተይዞ ፡ ቢመርቃቸው ፡ ምን ፡ ይረባ
ቸዋል ፡ ምን ፡ ይጠቅማቸዋል ፡ ፩ ፡ ዮሐ ፡
፫ ፡ ፲፯ ።

፲፯ ፤ ከማሁ ፡ ይእቲ ፡ ሃይማኖት ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡
ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ምዉት ፡ ይእቲ ፡ ለሊሃ ።

እንደዚሁም ፡ ምግባር ፡ የሌላት ፡ ሃይማ
ኖት ፡ የሞተች ፡ ናት ፡ አለ ፡ ሥራ አታ
ሠራም ።

፲፰ ፤ እመ ፡ ቦ ፡ ዘይቤለከ ፡ አንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ብከ ፡
ለከ ፡ ላንተ ፡ ሃይማኖት ፡ አለህ ፡ የሚልህ ፡
ሰው ፡ ቢኖር ፡

ወአነ ፡ ምግባረ ፡ ሠናየ ፡ ብየ ፡

ሊተ ፡ ለኔ ፡ ምግባር ፡ አለኝ ፡ የሚልህ ፡
ሰው ፡ ቢኖር ፡

አርእየኒኬ ፡ ሃይማኖተከ ፡ ዘእንበለ ፡ ምግባሪከ ፡

ሃይማኖትህን ፡ ከምግባርህ ፡ ለይተህ ፡ በዚ
ያው ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ አሳየኝ ፡ የሚልህ ፡
ሰው ፡ ቢኖር ፡ ምንተ ፡ ይበቍዖ ፡ ምዉት ፡
ይእቲ ፡ ላለው ፡ ምን ፡ ይረባዋል ፡ ምን ፡
ይጠቅመዋል ፡

ወአንሰ ፡ አርእየከ ፡ እምነ ፡ ምግባርየ ፡ ሃይማኖትየ ።

ምግባርየ ፡ እምነ ፡ ሃይማኖትየ ፡ እኔም ፡
ምግባሬን ፡ ከሃይማኖቴ ፡ ለይቼ ፡ በዚያው ፡
ሥራ ፡ ሠርቼ ፡ አሳይሃለሁ የሚልህ ፡ ሰ
ው ፡ ቢኖር ፡ በጎ ፡ እንጅ ፡ ነው ፡ (ሐተታ) ፡ ሃይ
ማኖት ፡ ያለ ፡ ምግባር ፡ ሥራ እንዳያ
ሠራ ፡ ምግባር ፡ ያለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሥራ ፡
ያሠራልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ይህ ፡
ሰው ፡ ሁሉንም ፡ ያልያዘ ፡ ነው ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ያለ ፡ ምግባር ፡ ሥራ ፡ እንዳያሠራ ፡
ምግባርም ፡ ያለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሥራ ፡ አያ
ሠራምና ፡ አስጨንቆ ፡ አስጠብቦ ፡ ከነገሩ ፡
ለማግባት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እንጅ ። አንድም ፡
(እመ ፡ ቦ ፡ ዘይቤለከ) ፡ ለከ ፡ ላንተ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ አለህ ፡ የሚልህ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡
(ሊ.ተ) ፡ ለኔ ፡ ምግባር ፡ አለኝ ፡ የሚልህ ፡
ሰው ፡ ቢኖር ፡ (ምግባርየ ፡ እምነ ፡ ሃይማ
ኖትየ ፡ ምግባሬን ፡ ከሃይማኖቴ ፡ ለይቼ ፡
በዚያው ፡ ሥራ ፡ ሠርቼ ፡ አሳይሃለሁ ፡ የሚ
ል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ (ምንተ ፡ ይበቍዖ) ፡ ምን ፡
ይረባዋል ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ። አንድም ፡
አይለወጥም ፡ ላንት ፡ ሃይማኖት ፡ አለህ ፡
ለኔ ፡ ምግባር ፡ አለኝ ፡ የሚልህ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡

ምግባሪከ ፡ እምነ ፡ ሃይማኖትከ ፡ (በሎ) ፡ ም
ግባርህን ፡ ከሃይማኖትህ ፡ ለይተህ ፡ በዚያው ፡
ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ አሳየኝ ፡ በለው ፡ (በሎ) ፡
እኔም ፡ ሃይማኖቴን ፡ ከምግባሬ ፡ ለይቼ ፡ በዚ
ያው ፡ ሥራ ፡ ሠርቼ ፡ አሳይሃለሁ ፡ በለው ።
አንድም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ካመኑ ፡ ከተጠ
መቁ ፡ ምን ፡ ምግባር ፡ ያሻል ፡ የሚል ፡
ሰው ፡ ቢኖር ፡ (ለከ) ፡ በሎ ፡ ላንት ፡ ሃይ
ማኖት ፡ አለህ ፡ በለው ፡ (ሊ.ተ) ፡ በሎ ፡
ለኔ ፡ ምግባር ፡ አለኝ ፡ በለው ፡ አርእየኒኬ ፡
ሃይማኖተከ ፡ ዘእንበለ ፡ ምግባሪከ ፡ በሎ ፡
ሃይማኖትህን ፡ ከምግባርህ ፡ ለይተህ ፡
በዚያው ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ አሳየኝ ፡ በለ
ው ፡ ምግባርየ ፡ እምነ ፡ ሃይማኖትየ ፡ በሎ ፡
እኔም ፡ ምግባሬን ፡ ከሃይማኖቴ ፡ ለይቼ ፡
በዚያው ፡ ሥራ ፡ ሠርቼ ፡ አሳይሃለሁ ፡
በለው ። አንድም ፡ (ሊ.ተ) ፡ ለኔ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ አለኝ ፡ የሚልህ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡
(ለከ) ፡ ላንት ፡ ምግባር ፡ አለህ ፡ የሚልህ ፡
ሰው ፡ ቢኖር ፡ በሎ ፡ ሃይማኖተከ ፡ ዘእን
በለ ፡ ምግባሪከ ፡ ሃይማኖትህን ፡ ከምግ
ባርህ ፡ ለይተህ ፡ በዚያው ፡ ሥራ ፡ ሠር
ተህ ፡ አሳየኝ ፡ በለው ፡ ምግባርየ ፡ እምነ ፡
ሃይማኖትየ ፡ (በሎ) ፡ እኔም ፡ ምግባሬን ፡ ከ
ሃይማኖቴ ፡ ለይቼ ፡ በዚያው ፡ ሥራ ፡ ሠ
ርቼ ፡ አሳይሃለሁ ፡ በለው ፡ ገላት ፡ ፭ ፡ ፮ ።

፲፱ ፤ አንተሰ ፡ ተአምን ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡
እግዚአብሔር ፡

አንተስ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ታምናለህ ፡

ሠናየ ፡ ትገብር ፡

በጎ ፡ አምነሃል ፡ ስማዕ ፡ እስራኤል ፡ አሐ
ዱ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡
ብሏልና ፡

ከማሁስ ፡ አጋንንትኒ ፡ የአምኑ ፡

እንደዚሁስ ፡ አጋንንትም ፡ ያምናሉ ፤ በአ
የሱስኒ ፡ አአምን ፡ ወለጳውሎስኒ ፡ አአ
ምሮ ፡ ይላሉና ፡

ወይደነግፁ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይደነግጣሉ ፡ መጻእከኑ ፡
ዝየኒ ፡ ትስድደነ ፡ ወዘእንበለ ፡ ጊዜሁ ፡
ትሣቅየኒ ፡ ብለውታልና ።

፳ ፤ ትፈቅድኑ ፡ ታእምር ፡ አ ፡ ብእሲ ፡ አብድ ፡ ከመ ፡
ሃይማኖት ፡ ዘእንበለ ፡ ምግባር ፡ ምዉት ፡ ይእቲ ፡

አንት ፡ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ሃይማኖት ፡ ያለ ፡
ምግባር ፡ ሥራ ፡ እንዲታሠራ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡
ስትማር ፡ ስትረዳ ፡ ልትኖር ፡ ትወዳለህን ፡

፳፩ ፤ አኮኑ ፡ አቡነ ፡ አብርሃም ፡ በምግባሩ ፡ ጸድቀ ፡
ሶበ ፡ አዕረገ ፡ ለይስሐቅ ፡ ወልዱ ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዕ ።

አባታችን ፡ አብርሃም ፡ ልጁ ፡ ይስሐቅን ፡
ለመሥዋዕትነት ፡ ባቀረበው ፡ ጊዜ ፡ በም
ግባሩ ፡ ከበረ ፡ የከበረ ፡ አይደለምን ፡ ዘፍጥ ፡
፳፪ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ።

፳፪ ፤ ትሬኢኑ ፡ ከመ ፡ ሃይማኖት ፡ ትረድኦ ፡ ለገቢር ፡

ሃይማኖት ፡ ለምግባር ፡ አጋዥ ፡ እንደ ፡
ሆነች ፡ ታያለህን ፡ ታውቃለህን ፡

ወበምግባሩ ፡ መልአ ፡ ወፍጹመ ፡ ኮነ ፡ ሃይማኖቱ ።

ሃይማኖቱ ፡ በምግባሩ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ
ለት ፡ ታያለህን ፡ (ፍጹም ፡ እንደ ፡ ሆነ
ለት ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ።

፳፫ ፤ ወተፈጸመ ፡ ዘይብል ፡ መጽሐፍ ፡ አምነ ፡
አብርሃም ፡ በእግዚአብሔር ፡

አብርሃም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመነ ፡

ወተኈለቈ ፡ ጽድቀ ፡

ማመኑ ፡ ጽድቅ ፡ ሁኖ ፡ ተነገረለት ፡ ከጽ
ድቅ ፡ ገብቶ ፡ ተቈጠረለት ፡

ወፍቁረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተሰምየ ።

ዐርከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተባለ ፡ ብሎ ፡
መጽሐፍ ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ደረሰ ፡
ተፈጸመ ፡ ሐተታ ፡ ከዚያ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በአንቀጸ ፡ አሚን ፡ በተአምኖ ፡ ወሰዶ ፡ አብርሃም ፡ ለይስሐቅ ፡ ወልዱ፡ ብሎ፡ ሃይ ማኖቱን ፡ መስክሮለታል ፡ ከዚህም ፡ ያዕ ቆብ ፡ በአንቀጸ ፡ ምግባር ፡ አኮኑ ፡ አቡነ ፡ አብርሃም ፡ በምግባሩ ፡ ጸድቀ ፡ ብሎ ፡ ምግባሩን ፡ መስክሮለት ፡ ዘፍጥ ፡ ፲፭፡፮ ። ኢሳ ፡ ፵፩ ፡ ፰ ።

፳፬ ፤ ትሬኢኑ ፡ ከመ ፡ በምግባሩ ፡ ይጸድቅ ፡ ሰብእ ፡ ወአኮ ፡ በሃይማኖቱ ፡ ባሕቲታ ፡

ሰው ፡ በሃይማኖቱ ፡ ብቻ ፡ ያይደለ ፡ በም ግባሩ ፡ እንዲከብር ፡ ታያለህን ፡

፳፭ ፤ ወከማሁ ፡ ረዓብኒ ፡ ዘማ ፡ በምግባሪሃ ፡ ጸድቀት ።

አብርሃም ፡ በምግባሩ ፡ ከበረ ፡ እንዳልሁ ፡

ሶበ ፡ ተቀበለቶሙ ፡ ለሰብአ ፡ ዐይን ፡ ወአንተ ፡ ካል እት ፡ ፍኖት ፡ አውፅአቶሙ ።

ረዓብ ፡ ዘማም ፡ የእስራኤልን ፡ ጉበኞች ፡ በፍቅር፡ ተቀብላ ፡ በፍቅር ፡ ሸኝታ፡ በሰደ ደቻቸው፡ ጊዜ ፡ በሙያዋ ፡ በሥራዋ ፡ እን ደ ፡ ከበረች ፡ ታያለህን ። ሐተታ ፡ ከዚያ ፡ በአንቀጸ ፡ አሚን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ረዓብኒ ፡ ዘማ፡ በተአምኖ ፡ ኢተሐጕለት ፡ ምስለ ፡ አላውያን ፡ ብሎ ፡ ሃይማኖቷን ፡ መስክሮላታል ፡ ከዚህም ፡ ያዕቆብ ፡ በአ ንቀጸ ፡ ምግባር ፡ አኮኑ ፡ ረዓብኒ ፡ ዘማ ፡ በምግባሪሃ ፡ ጸድቀት ፡ ብሎ፡ ምግባሯን ፡ መስክሮላት ፡ ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፴፩ ።

፳፮ ፤ በከመ ፡ ሥጋ ፡ ዘአልቦ ፡ መንፈስ ፡ ምውት፡ ውእቱ ፡ ከማሁ ፡ ሃይማኖትኒ ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ምዉት ፡ ይእቲ ።

ነፍስ ፡ የተለየው ፡ ሥጋ ፡ ሥራ ፡ እንዳ ይሠራ ፡ ምግባር ፡ የሌላትም ፡ ሃይማኖት ፡ ሥራ ፡ አታሠራም ፡ ቍ ፡ ፲፯ ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ፤ ወኢይኩኑ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ ብዙኃን ፡ መምህራን ፡

ከዚህም ፡ በሹመት ፡ ተቃንተዋል ፡ ለዚህ፡ ያመጣል ፡ ከናንተ ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ መም ህራን ፡ አይኑሩ ። አንድም ፡ መምህራን ፡ ብዙኃን ፡ መምህራን ፡ አይብዙ ። አን ድም ፡ ብዙኃን ፡ መምህራን ፡ ብዙ ፡ ሰዎ ች ፡ መምህራን ፡ አይሁኑ ፡ (አይሾሙ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡

አኀዊነ ፡ ተአምሩ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ተዐቢ ፡ ደይነ ፡ ንነሥእ ።

ወንድሞቻችን ፡ እንሾም ፡ በማለት ። አን ድም ፡ በመሾም ፡ ተሹመን ፡ በመበደል ፡ ጽኑ ፡ ፍዳ ፡ እንድንቀበል ፡ ታውቃላችሁ ፡

፪ ፤ እስመ ፡ ብዙኀ ፡ ንስሕት ፡ ኵልነ ፡

ሁላችን፡ ፈጽመን፡ እንበድላለንና። አንድ፡ ም ፡ ፈጽመን ፡ ስለ ፡ በደልን ፡ጽኑ ፡ ፍዳ፡ እንድንቀበል ፡ ታውቃላችሁና፡ ኢይኩኑ፡ ላለው ፡

ወዘሰ ፡ ኢይስሕት ፡ በቃሉ ፡ ፍጹም ፡ ውእቱ ፡

ልሾም ፡ በማለት ። አንድም ፡ በመሾም ፡ ተሹሞ ፡ የማይበድል ፡ ፍጹም ፡ ነው ፡

ወይክል ፡ ወድዮ ፡ ልጓም ፡ ለኵሉ ፡ ሥጋሁ ።

ለሰውነቱ ፡ ልጓመ ፡ ትዕግሥትን ፡ ገን ዘብ ፡ ማድረግ ፡ ይቻለዋል ። አንድም ፡ የሚቻለው ፡ ፍጹም ፡ ነው ። (ታሪክ) ፡ እንደ ፡ አባ ፡ መቃርዮስ ፡ በሕፃንነቱ ፡ መንኖ ፡ ገዳም ፡ ገብቷል ፡ ኋላም ፡ መብ ቃቱን ፡ አይተው ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ ሹመውታል ፡ እናቴን ፡ የምስ ራች ፡ ተሾምሁ፡ ብላችሁ ፡ ንገሯት፡ ብሎ፡ ሰው ፡ ላከ ፡ ሂደው ፡ ባነገሯት ፡ ቀና

ብላ ፡ መልስ ፡ ሳትመልስላቸው ፡ ቀረች ፤ ተመልሰው ፡ ሄዱ ፡ ምን ፡ ብላ ፡ ሰደደቻ ችሁ ፡ አላቸው ፡ ለኛስ ፡ መልስም ፡ አል መለሰችልንም ፡ አሉት ፡ የእናቴ ፡ ነገር ፡ እኔን ፡ እንጅ ፡ ያልመጣ ፡ ብላ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አልባሰ ፡ ሢመቱን ፡ ለብሶ ፡ ማኅ በሩን ፡ አስከትሎ ፡ ሂዶ ፡ እናቴ ፡ የምስ ራች ፡ ተሾምሁ ፡ አላት ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ ሳታ የው ፡ ቀረች ፡ ምነው ፡ እናቴ ፡ አላወቅሽ ኝም ፡ እኔ ፡ እንጅ ፡ ልጅሽ ፡ ነኝ ፡ አላት ፡ አንተ ፡ አላወቅህም ፡ እንጅ ፡ እኔስ ፡ አው ቄሃለሁ ፡ ዛሬ ፡ በአልባሰ ፡ ሢመት ፡ አም ረህ ፡ አጊጠህ ፡ ካይህ ፡ በልብስ፡ መግነዝ ፡ ተተብትበህ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ስትወ ርድ ፡ ባይህ ፡ በተሻለኝ ፡ ነበር ፡ አለችው፤ ደንግጦ ፡ ምነው ፡ እናቴ ፡ አላት ፡ እስካ ሁን ፡ በራስህ ፡ ኃጢአት ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ እንግዲህማ ፡ በሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ሊፈረድብህ ፡ አይደለምን ፡ አለችው ፡ ይህ ፡ የናቴ ፡ ቃል ፡ ተግሣፅ ፡ ሆኖኝ ፡ እስ ከሞት ፡ ድረስ ፡ ከማስተማር ፡ አላረፍ ሁም ፡ ብሏል ።

፫ ፤ ወናሁ ፡ ለአፍራስኒ ፡ ንወዲ ፡ ሎቶን ፡ ልጓመ ፡ ውስተ ፡ አፉሆን ፡

እነሆ ፡ ፈረሶችን ፡ በአፋቸው ፡ ልጓም ፡ እናጎርሳቸዋለን ።

ከመ ፡ አሆ ፡ ይበላነ ፡

ዐቀበቱን ፡ ውጡ ፡ ሜዳውን ፡ ሩጡ ፡ ብንላቸው ፡ እሺ ፡ በጄ ፡ ይሉን ፡ ዘንድ ፡

ወንመይጦን ፡ ኵሎ ፡ ሥጋሆን ።

ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ እንመልሳቸዋለን ፡ መዝ ፡ ፴፪ ፡ ፱ ።

፬ ፤ ወናሁ ፡ ለአሕማርኒ ፡ ዘመጠነ ፡ ዝ፡ አካሎን ፡ በኀይለ ፡ ነፋስ ፡ ሶበ ፡ ይትነድአ ፡ ወይትመየጣ ።

አካሉን ፡ ግዘፎን ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ግዘፉ ቸው ፡ ይህን፡ ያህል ፡ የሚሆን፡ መርከቦች ንም ። (ሐተታ) ፡ ታናሽቱ ፡ የጳውሎስ ፡ መርከብስ ፡ እንኳ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰብ ዓ ፡ ስድስት ፡ ሰው ፡ ይዛ ፡ ነበር ፡ ነፋስ፡ በወሰዳቸው ፡ ጊዜ ፡

ይመይጦን ፡ ብእሲ ፡ በሐዳፍ ፡ እንዘ ፡ መጠነ ፡ ዝ ፡ ናእሱ ፡

መጠኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ሲሆን ፡ ማለት ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር ፡ የሚሆን ፡ ሲሆን ፡ ቀዛፊ ፡ ይመልሳቸዋል ። አንድም፡ (በሐዳፍ ፡ ዘመጠነ ፡ ዝ) ፡ መጠኑ ፡ ይህን፡ ያህል ፡ በሚሆን ። አንድም ፡ ይህን ፡ ያ ህል ፡ ሲሆን ፡ ትርከዛ ፡ ይመልሳቸዋል ። (ሐተታ) ፡ ብትር ፡ የሚቈረጥ ፡ በሰው ፡ ቁመት ፡ ልክ ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር ፡ ነውና ፡ ዘመጠነ ፡ ዝ ፡ አለ ፡

ወያበውእን ፡ ውስተ ፡ መርሶ ፡ ኀበ ፡ ፈቀደ ።

ወደ ፡ ወደደው ፡ ወደብ ፡ ያደርሳቸዋል ።

፭ ፤ ከማሁ ፡ ልሳንኒ ፡ ንስቲት ፡ አባል ፡ ይእቲ ፡

ልሳንም ፡ ታናሽ ፡ ሕዋስ ፡ ናት ፡ ከማሁ ፡ (ልጓም ፡ ናእስ ፡ ላለው ፡ ነው) ።

ወታመጽእ ፡ ዐቢያተ ፡

ጽኑ ፡ ጽኑ ፡ ነገርን ፡ ትናገራለች ፡

ወናሁ ፡ እሳትኒ ፡ ንስቲት ፡ ጥቀ ፡

እነሆ ፡ እሳትም ፡ ከቡላድ ፡ ስትወጣ ፡ እ ጅግ ፡ ታናሽ ፡ ናት ፡

ዘመጠነ ፡ ዝ ፡ ያመ ፡ ታውዒ ፡

ይህን ፡ ያህል ፡ ባንባውን ፡ ዋርካውን ፡ ታቃጥላለች ።

፮ ፤ ወልሳንኒ ፡ እሳት ፡ ይእቲ ፡ ለዓለም ፡ ዘዐመፃ ፡

ልሳን ፡ ዘዐመፃ ፡ (ብለህ ፡ ግጠም) ፡ ዐሙ ፅን ፡ የምትናገር ፡ አንደበትም ፡ ለሰው ፡ እጥፊ ፡ ናት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወናሁ ፡ ልሳንኒ ፡ ተፈጥረት ፡ ውስተ ፡ ነፍስትነ ፡

እነሆ ፡ እንደበት ፡ በሰውነታችን ፡ ውስጥ ፡ በጉሮሯችን ፡ ተፈጥራለች ፡

ወታረምዮ ፡ ለሥጋነ ፡

ሥጋችንን ፡ ታቃጥለዋለች ፡

ወትሌሉ ፡ ክቡተ ፡ ፍጥረትነ ፡

ካራት ፡ ባሕርያት ፡ የተፈጠረ ፡ ሰውነታችንን ፡ ትለበልበዋለች። አንድም ፡ትሴሊ ፡ ቢል ፡ ነፍሳችንን ፡ ከሥጋችን ፡ ትለያለች ፡

ወታውዒ ፡ እምገሃነም ፡

ከገሃነም ፡ አስቀድማ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ። አንድም ፡ ከገሃነም ፡ ይልቅ ፡ ታቃጥላለች ፡ ሐተታ ፡ ገሃነም ፡ ኃጥአንን ፡ እንጅ ፡ ጻድቃንን፡ አታቃጥልም፡ አንደበት፡ ግን ፡ ኃጥኡንና ፡ ጻድቁን ፡ አትለይምና ። አንድም ፡ በገሃነም ፡ ታቃጥላለች ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ና ፡ ፲፱ ። ም ፡ ፲፪ ፡ ፴፮ ፡ ፴፯ ።

፯ ፤ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ አራዊትኒ ፡

ያራዊት ፡ ባሕርይ ፡

ወአዕዋፍኒ ፡

የአዕዋፍም ፡ ባሕርይ ፡

ወዘይትሐወስኒ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡

በባሕር ፡ የሚመላለስ ፡ ያዞ ፡ የጉማሬ ፡ የዓሣ ፡ የአንበሪ ፡ ባሕርይ ፡

ወእንስሳኒ ፡

የእንስሳም ፡ ባሕርይ ፡ ሁሉ ፡

ይገርር ፡ ለፍጥረተ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ።

ለሰው ፡ ባሕርይ ፡ ይገዛል ፡ እኮን ።

፰ ፤ ወለልሳነ ፡ እጓለ ፡ እመሕያውሰ ፡ አልቦ ፡ ዘይክል ፡ አግርሮታ ፡

የሰውን ፡ አንደበት ፡ ግን ፡ ሊገዛት ፡ ሊገታት ፡ የሚቻለው ፡ የለም ፡

እኪት ፡ ይእቲ ፡

ክፉ ፡ ናት ፡

ወአልባ ፡ ዐቅም ፡

ለክፋቷም፡ ልክ፡ መጠን ፡ የለውም ። አንድም ፡ ክንድ ፡ ስንዝር ፡ አትባልም ፡

ወምልእት ፡ ይእቲ ፡ ሐምዘ ፡ ዘይቀትል ።

የሚገል ፡ መርዝን ፡ የተመላች ፡ ናት ፤ አለ ፡ መርዝ ፡ እንዲጎዳ ፡ የምትጎዳ ፡ ናት ። መዝ ፡ ፻፵ ፡ ፬ ።

፱ ፤ ባቲ ፡ ንባርኮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ወባቲ ፡ ንረግሞ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘበአርአያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተፈጥረ ።

በአንደበት ፡ ወዲህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመሰግነዋለን ፤ ወዲህ ፡ በአርአያ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተፈጠረ ፡ ሰውን ፡ እንሰድበዋለን ። (ሐተታ) ፡ ዘበአርአያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተፈጥረ ፡ አለ ፡ በቅርጽ ፡ ነው ፡ (ጥቅ)፡ ነአምን፡ ከመ፡ ቦ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አዕይንት፡ ወአዕዛን፡ አዕዳው ፡ ወእገር ፡ ወኵሎንከ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ አባላት ፡ እንዲል ። አንድም ፡ በነፍስ ፡ ነው ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ለባዊት ፡ ሕያዊት ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ሥላሴም ፡ ነባብያን ፡ ለባውያን ፡ ሕያዋን ፡ ናቸውና ። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ በባሕርዩ ፡ የሚገዛውን ፡ ሰው ፡ በጸጋ ፡ ይገዛዋልና ፡ (ጥቅ) ፡ ወበከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርኡስ ፡ ወሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወታሕተ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ከማሁ ፡ ሰብእኒ ፡ ርኡስ ፡ ወሥሉጥ ፡ ታሕተ ፡ ውስተ ፡ ምድር፡ እንዲል ፡ ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ።

፲ ፤ እምአሐዱ ፡ አፍ ፡ ይፃእ ፡ ቡራኬ ፡ ወመርገም ፡ ኢይረትዕ ፡ ከመዝ ፡ አኀዊነ ፡ ይኩን ።

ይረትዕና ፡ ይኩን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ወንድሞቻችን ፡ ባንድ ፡ አንደበት ፡ ወዲህ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርን ፡ ማመስገን ፡ ወዲህ ፡ በአርአያ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተፈጠረ ፡ ሰውን ፡ መሳደብ ፡ አይገባም ።

፲፩ ፤ ይትከሃልኑ ፡ ይፃእ ፡ እምአሐዱ ፡ ዐይን ፡ ወእምውስተ ፡ አሐቲ ፡ ዐዘቅት ፡ ይነቅዕኑ ፡ ማይ ፡ መሪር ፡ ወማይ ፡ ጥዑም ።

ካንድ ፡ ምንጭ ፡ ካንድ ፡ ጉድጓድ ፡ ማይ ፡ መሪር ፡ ማይ ፡ ጥዑም ፡ ሊወጣ ፡ ይቻላልን ፡ (ሐተታ) ፡ ማይ ፡ ጥዑም ፡ በሀገራችን ፡ የሚጠጣው ፡ ነው ፡ ማይ ፡ መሪር ፡ አምቦ ፡ ነው ፡ ይህስ ፡ ምግብነት ፡ ያለው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ባሕረ ፡ ጌው ፡ ነው ፡ በሀገራቸው ፡ ማይ ፡ ጥዑም ፡ የሚጠጣው ፡ ነው ።

፲፪ ፤ ይክልኑ ፡ አኀዊነ ፡ በለስ ፡ ዘይተ ፡ ፈርየ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ወይን ፡ በለሰ ፡ ፈርየ ፡

ወንድሞቻችን ፡ በለስ ፡ ዘይትን ፡ ወይን ፡ በለስን ፡ ማፍራት ፡ ይቻለዋልን ፡ ማለት ፡ በለስ ፡ ዘይትን ፡ ወይን ፡ በለስን ፡ ማፍራት ፡ እንዳይቻለው ፡

ከማሁኬ ፡ ማይኒ ፡ መሪር ፡ ኢይከውን ፡ ጥዑመ ፡ ወማይኒ ፡ ጥዑም ፡ ኢይከውን ፡ መሪረ ።

ማይ ፡ መሪር ፡ ማይ ፡ ጥዑምን ፡ ማይ ፡ ጥዑም ፡ ማይ ፡ መሪርን ፡ አይሆንም ፡ እንደዚህም ፡ ነቢየ ፡ ጽድቅ ፡ ነቢየ ፡ ሐሰትን ፡ ነቢየ ፡ ሐሰት ፡ ነቢየ ጽድቅን ፡ አይሆንም ።

፲፫ ፤ ወመኑ ፡ ጠቢብ ፡ እምኔክሙ ፡ ወምሁር ፡

ከናንተ ፡ ወገን ፡ በዕውቀት ፡ የተፈተነ ፡ ብልህ ፡ ዐዋቂ ፡ ማነው ።

ከመ ፡ ያርኢ ፡ ምግባሮ ፡ በየዋሀት ፡ ወበጥበብ ፡ እምሥነ ፡ ግዕዙ ።

ከበጎ ፡ ግብሩ ፡ የተነሣ ፡ ባለመቃወም ፡ በፈሊጥ ፡ ሁኖ ፡ ሥራውን ፡ ይገልጽ ፡ ዘንድ ፡ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ። ም ፡ ፪ ፡ ፲፫ ።

፲፬ ፤ ወእመሰ ፡ ተቃንአ ፡ መሪር ፡ ወካህድ ፡ ቦክሙ ፡ ውስተ ፡ ልብክሙ ፡

የሚያሳዝን ፡ መቃናት ፡ ፀብ ፡ ክርክር ፡ በልቡናችሁ ፡ ካለባችሁ ፡

ኢትትመክሑ ፡

ወንጌላውያን ፡ ነን ፡ አትበሉ ፡

ወኢትሐስውዋ ፡ ለጽድቅ ።

ወንጌልንም ፡ አታሳብሏት ፡ ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፴፩ ፤

፲፭ ፤ ኢኮነት ፡ ዛቲ ፡ ጥበብ ፡ እንተ ፡ እምላዕሉ ፡ ትወርድ ፡

ይህች ፡ መቃናት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘች ፡ ጥበብ ፡ አይደለችም ፡

አላ ፡ እምድር ፡ እንተ ፡ እምነፍስ ፡ አጋንንት ።

ከአጋንንት ፡ ባሕርይ ፡ ነቅታ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በቃኤል ፡ ተጀምራለች ፡ እንጅ ። ም ፡ ፩ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።

፲፮ ፤ እስመ ፡ ኀበ ፡ ሀለወ ፡ ተቃንአ ፡ ሀየ ፡ ሀለወ ፡ ሀውክ ፡ ወካሕድ ፡

መቃናት ፡ ካለ ፡ ዘንድ ፡ ከዚያ ፡ ፀብ ፡ ክርክር ፡ አለና ፡

ወኵሉ ፡ እከየ ፡ ምግባር ።

ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አለና ፡

፲፯ ፤ ወእንተሰ ፡ እምላዕሉ ፡ ጥበብ ፡ ቀዳሚሃ ፡ ንጽሕት ፡ ይእቲ ፡

ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘች ፡ ደገኛ ፡ ጥበብስ ፡ አእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ናት ። አንድም ፡ አሪት ፡ ናት ፡

እንተ ፡ ታስተሰናሉ ፡

ሰውን ፡ ከሰው ። አንድም ፡ ሰውን፡ ከእግዚአብሔር ፡ የምታስማማ ፡

ወእንተ ፡ በዐቅም ፡ እሆ ፡ በሃሊት ፡

ያለ ፡ ልክ ፡ እሽ ፡ በጄ ፡ የምታሰኝ ፡

ወምልእት ፡ ምሕረተ ፡

ቸርነትን ፡ የተመላች ፡

ወፍሬሃ ፡ ሠናይ ፡

ሥራቷም ፡ ኢታምልክ ፡ ነው ፡

ዘእንበለ ፡ ኑፋቄ ፡ አማኒት ።

ያለጥርጥር ፡ የምታሳምን ።

፲፰ ፤ ወፍሬሃ ፡ ዘጽድቅ ፡ በሰላም ፡ ይዘራዕ ፡ ለእለ ፡ ይገብርዋ ፡ ለሰላም ።

ይዘራዕ ፡ በሰላም ፡ ይገብርዋ ፡ በሰላም ። ፍቅር ፡ የሚሆን ፡ ሥራዋም ፡ ፍቅርን ፡ ለያዙ ፡ ሰዎች ፡ በፍቅር ፡ ይሠራል ። አንድም ፡ (ወእንተሰ) ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘች ፡ ጥበብስ ፡ በቅድምና ፡ የነበረች ፤ ወልድ ፡ ናት ። አንድም ፡ ወንጌል ፡ ናት ፡ ለወልድ ፡ (ጥቅ) ፡ ቀዳሚሁ ፡ ቃል ፡ ውእቱ ፡ እንዲል ። ሰውን ፡ ከሰው ። አንድም ፡ ሰውን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የምታስማማ ፡ እጅሽን ፡ እግርሽን ፡ ለተሳለ ፡ ቀኖት ፡ አፍሽን ፡ ለምረረ ፡ ሐሞት ፡ ስጭልን ፡ ቢሏት ፡ እሺ ፡ በጄ ፡ የምትል ፡ ቸርነትን ፡ የተመላች ፡ ሥራቷም ፡ አፍቅር ፡ ቢጸክ ፡ ነው ፡ (ኢታምልክ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ያለጥርጥር ፡ የምታሳምን ፡ ናት ፡ አርአያ ፡ እግዚአብሔር ፡ አክባሪት ፡ ኵሉ ፡ ወልድ ፡ በሁሉ ፡ አድራ ፡ ሁሉን ፡ ራሷን ፡ ታስመስላለች ፡ ኢሳ ፡ ፴፪ ፡ ፲፯ ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ ፤ እምአይቴ ፡ ለክሙ ፡ ፀብእ ፡ ወቀትል ፡

ይህ ፡ ፀብ ፡ ክርክር ፡ ከወዴት ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡

አኮኑ ፡ እምዝየ ፡ እምአፍቅሮ ፡ ዝሙት ፡ ዘይትገበር ፡ ውስተ ፡ አንጕዕክሙ ።

በቅልጥማችሁ ፡ የሚሠራ ፡ (በሰውነታችሁም ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ዝሙትን ፡ ከመውደድ ፡ የተነሣ ፡ አይደለምን ፡ (ሐተታ) ፡ የበሉት ፡ የጠጡት ፡ ደም ፡ ይሆናል ፡ ቅልጥም ፡ ይመላል ፡ ይፈላል ፡ ልውጣ ፡ ልውጣ ፡ ይላልና ። (አውጡኝ ፡ አውጡኝ ፡ ይላል ፡ ቢሉም ፡ አንድ ፡ ነው) ። ዘይትገበር ፡ ውስተ ፡ አንጕዕክሙ ፡ አለ ፡ ሕ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

፪ ፤ ትፈትዉ ፡ ወኢትረክቡ ፡

ሹመቱን ፡ ሽልማቱን ፡ ትሻላችሁ ፡ አታገኙም ።

ትትቃተሉሂ ፡ ወትትቃንኡሂ ፡

ትጣላላችሁ ፡ ትቃናላችሁና ፡

ወኢትክሉ ፡ ረኪበ ፡

ስለዚህ ፡ ተሹሞ ፡ ከንዴተ ፡ ሥጋው ፡ መዳን ፡ አይቻላችሁም ፡

ትትበአሱሂ ፡ ወትትፃብኡሂ ፡ ወኢትረክቡ ፡ እስመ ፡ ኢትስእሉ ።

ትጣላላችሁ ፡ አታገኙም ፡

ይኩን ፡ ፈቃድከ ፡ ብላችሁ ፡ አትለምኑምና ።

፫ ፤ ትስእሉሂ ፡ ወኢይሁቡክሙ ፡

መለመኑንስ ፡ ትለምናላችሁ ፡ ፍትሑ ፡ ርቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ አይሰጥዋችሁም ፡ እንጅ ፡

እስመ ፡ እኪተ ፡ ትስእሉ ፡ ለዝሙትክሙ ።

ኃጢአታችሁን ፡ ታበረክቱ ፡ ዘንድ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ትለምናላችሁና ። አንድም ፡ (ትፈትዉሂ) ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ልትገቡ ፡ ትወዳላችሁ ፡ አትገቡም ፡ (ትትቃተሉሂ) ፡ ትጣላላችሁ ፡ ትቃናላችሁና ፡ (ወኢትክሉ) ፡ ስለዚህ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ገብቶ ፡ ከንዴተ ፡ ጺጋው ፡ መዳን ፡ አይቻላችሁም ፡ (ትትበአሱሂ) ፡ ትጣላላችሁና ፡ አትገቡም ፡ (እስመ ፡ ኢትስእሉ) ፡ ትምጻእ ፡ መንግሥትከ ፡ ብላችሁ ፡ አትለምኑምና ፡ (ትስእሉሂ) ፡ መለመኑንስ ፡ ትለምናላችሁ ፡ ፍትሑ ፡ ርቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ አይሰጥዋችሁም ፡ እንጅ ፤ (እስመ ፡ እኪተ) ፡ ሰውነታችሁን ፡ ለሰይጣን ፡ ታሳብሩ ፡ ዘንድ ፡ የማይገባ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ትለምናላችሁና ፡ (ጥቅ) ፡ ንሕነሰ ፡ ኢተወለድነ ፡ እምዝሙት ፡ እንዲል ፡ መዝ ፡ ፲፰ ፡ ፵፪ ።

፬ ፤ አ ፡ ዘማውያን ፡ ኢተአምሩኑ ፡ ፍቁሩ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡ ወጸላኢሁ ፡ ውእቱ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እናንተ ፡ ዘማውያን ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ወዳጆች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጠላቶች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አታውቁምን ። አንድም ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ወዳጆች ፡ ዘማውያን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጠላቶች ። አንድም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጠላቶች ፡ ዘማውያን ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ወዳጆች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አታውቁምን ፡

እስመ ፡ ዘአብደረ ፡ ፍቅሮ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡ ጸላኢሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይከውን ።

ይህን ፡ ዓለም ፡ የወደደ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡ ይለያልና ፡ ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፳፯ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፯ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ።

፭ ፤ ወሚመ ፡ ይመስለክሙኑ ፡ ዘሐሰተ ፡ ይብል ፡ መጽሐፍ ፡ ከመ ፡ ተቃንአ ፡ ያፈቅር ፡ መንፈስ ፡ ዘየኀድር ፡ ላዕሌክሙ ።

ወይስ ፡ በናንተ ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ ሰይጣን ፡ ሀብተ ፡ ቅናትን ፡ እንዲወድ ፡ ዐውቆ ፡ ኢትቅናዕ ፡ ላዕለ ፡ እኩያን ፡ ወኢትቅናዕ ፡ ላዕለ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ፡ እስመ ፡ ሥዩም ፡ እከይ ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ፡ ያለ ፡ መጽሐፍ ፡ በሐሰት ፡ ይመስላችኋልን ። አንድም ፡ በናንተ ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅንአትን ፡ ወዶ ፡ ሳለ ፡ መጽሐፍ ፡ በሐሰት ፡ ቅንአት ፡ ኢይብቋዕ ፡ ያለ ፡ ይመስላችኋልን ፡ ገላት ፡ ፭ ፡ ፲፯ ።

፮ ፤ ወባሕቱ ፡ እምላክነ ፡ እንተ ፡ ተዐቢ ፡ ሞገሰ ፡ ይሁበነ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ እንሾም ፡ ባንል ። አንድም ፡ ባንሾም ፡ ፈጣሪያችን ፡ የበለጠች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ይሰጠናል ፡

ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ለዕቡያን ፡ ይትሄየዮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡

ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ትቢተኞችን ፡ ቸል ፡ ይላቸዋል ።

ወለእለሰ ፡ ያቴሕቱ ፡ ርእሶሙ ፡ ይሁቦሙ ፡ ሞገሰ ።

ራሳቸውን ፡ የሚያዋርዱትን ፡ ግን ፡ ያከብራቸዋል ፡ ቃሉ ፡ ቃለ ፡ ሐና ፡ ነው ፡ ሲ ውጦ ፡ እነበበው ፡ ኢዮብ ፡ ፳፪ ፡ ፳፱ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፲፪ ።

፯ ፤ አሆ ፡ በልዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ እሺ ፡ በጄ ፡ በሉት ፡

ወእንብዩ ፡ በልዎ ፡ ለጋኔን ፡

ሰይጣንን ፡ ግን ፡ እሺ ፡ በጄ ፡ አትበሉት ፡

ወይጐይይ ፡ እምኔክሙ ።

ይርቅላችኋል ፡ ኤፌ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ።

፰ ፤ ቅረብዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወይቀርበክሙ ፡

እግዚአብሔርንስ ፡ ብንቀርበው ፡ ይቀርበናልን ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔርንስ ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ ቅረቡት ፡ ይቀርባችኋል ፡

አንጽሑ ፡ እደዊክሙ ፡ ኃጥአን ፡ ወአንጽሑ ፡ ልበክሙ ።

ኃጥአን ፡ እደ ፡ ሥጋችሁን ፡ ከመግደል ፡ እደ ፡ ቃላችሁን ፡ ከመበደል ፡ ልዩ ፡ አድርጉ ፡ (ወአንጽሑ ፡ ልበክሙ) ፡ ልቡናችሁን ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ንጹሕ ፡ አድርጉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እለ ፡ ትናፍቁ ፡ ግነዩ ።

የምትጠራጠሩም ፡ አምስቱን ፡ አዕማደ ፡ ምሥጢር ፡ ዕመኑ ፡ ዘካ ፡ ፩ ፡ ፫ ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ።

፱ ፤ ወላሕዉ ፡ ወብክዩ ።

እዘኑ ፡ አልቅሱ ፡

ወለሰሐቅክሙኒ ፡ ሚጥዎ ፡ ውስተ ፡ ላሐ ፡

ሳቃችሁን ፡ ወደ ፡ ልቅሶ ፡ መልሱት ፡

ወለተፍሥሕትክሙኒ ፡ ውስተ ፡ ትካዝ ፡ አግብእዎ ፡

ደስታችሁንም ፡ ወደ ፡ ኀዘን ፡ መልሱት ፡ ማለት ፡ ሳቁን ፡ ትታችሁ ፡ አልቅሱ ፡ ተድላ ፡ ደስታውን ፡ ትታችሁ ፡ እዘኑ ፡

፲ ፤ አትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ።

ትሕትናን ፡ ያዙ ፡

ወያሌዕለክሙ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ልዕልና ፡ ነፍስን ፡ ሰጥቶ ፡ ያከብራችኋል ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

፲፩ ፤ ወኢትትሐመዩ ፡ በበይናቲክሙ ፡

እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ አትነቃቀፉ ፡

አኀዊነ ።

ወንድሞቻችን ፡

እስመ ፡ ዘሐመየ ፡ ለካልኡ ፡ ሐመየ ፡ ለሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዘይግዕዞ ፡ ካልአ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገዐዘ ።

ዘሐመየ ፡ ለካልኡና ፡ ሐመየ ፡ ለሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዘይግዕዝ ፡ ካልእና ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገዐዘ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ ወንድሙን ፡ የሚነቅፍ ፡ ሰው ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይነቅፋልና ፡

ወእመሰ ፡ ሕጎ ፡ ትግዕዝ ፡

ሕጉን ፡ የምትነቅፍ ፡ ከሆነ ፡

ኢኮንከ ፡ ገባሬ ፡ ሕግ ፡

ፈጻሜ ፡ ሕግ ፡ አይደለህም ፡

አላ ፡ ኮንከ ፡ ገዐዚሁ ፡ ለሕግ ።

ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ ነህ ፡ እንጅ ፡ መዝ ፡ ፲፰ ፡ ፫ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፩ ።

፲፪ ፤ እስመ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ ወሀቢሃ ፡ ለሕግ ፡

ሕግን ፡ የሚሠራ ፡ የሚያፈርስ ፡

ወመኰንና ፡ ለሕግ ፡

የሚፈርድ ፡ አንድ ፡ እሱ ፡ ነውና ፡

ዘውእቱ ፡ ይክል ፡ አግስኖሂ ፡ ወአድኅኖሂ ፡

ማዳን ፡ መግደል ፡ የሚቻለው ፡ ብሎ ፡ ለጌታም ፡ ለሕጉም ፡ ይቀጥላል ፡

አንተኬ ፡ ምንትኑ ፡ አንተ ፡ ዘትግዕዞ ፡ ለካልእከ ፡

አንተ ፡ ወንድምህን ፡ የምትነቅፈው ፡ ምንድር ፡ ነህ ፡ መንግሥት ፡ ተበላላሚ ፡ ነህን ፡ ወረኛ ፡ ተነሥተሃልን ፡ ምስለኔውን ፡ ነህ ፡ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፩ ።

፲፫ ፤ ከመ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ዮም ፡ አው ፡ ጌሠመ ፡ ነሐውር ፡ ውስተ ፡ እንታክቲ ፡ ሀገር ፡ ወንነብር ፡

ቢሆን ፡ ዘንድሮ ፡ ባይሆን ፡ ከርሞ ፡ ከዚያች ፡ ሀገር ፡ ሂደን ፡ እንኖራለን ፡

ወንትጌበር ፡

ወጥተን ፡ ወርደን ፡ ነግደን ፡ አርሰን ፡ ቆፍረን ፡

ወንረብሕ ፡

ከብት ፡ አርብተን ፡ ቤት ፡ ሠርተን ፡ ንብረት ፡ ገዝተን ፡ እንኖራለን ፡ እንደሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ምሳ ፡ ፳፯ ፡ ፩ ።

፲፬ ፤ ወኢየአምሩ ፡ ዘይከውን ፡ ጌሠመ ፡

ከርሞ ፡ የሚሆነውን ፡ እንደማያውቁ ፡ እሳቸው ፡ ይሞቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይሞቱም ፡ እንደ ፡ ሆነ ። አንድም ፡ ያች ፡ አገር ፡ ከርሞ ፡ ትፈታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አትፈታም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደማያውቁ ፡

ምንትኑመ ፡ ሕይወትክሙ ፡

እንዲህማ ፡ ትሉ ፡ ዘንድ ፡ አነዋወራችሁ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡

እኮኑ ፡ ከመ ፡ ጢስ ፡ አንትሙ ፡ ዘለምዕር ፡ ያስተርኢ ፡ ወእምድኅሬሁ ፡ ይማስን ።

ጢስ ፡ ከጉድጓዱ ፡ ሲወጣ ፡ በዝቶ ፡ እንዲታይ ፡ ከመታየቱ ፡ ቀጥሎ ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲጠፋ ፡ እንደዚያ ፡ አይደላችሁምን ፡ ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፳ ።

፲፭ ፤ ዘእምትቤሉ ፡ እመ ፡ ወምረ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔር ፡ ቢፈቅድልን ፡

ወሐየውነ ፡

በንኖር ፡

ንገብር ፡ ዘንተ ፡

ከዚያች ፡ አገር ፡ መሄዱን ፡

አው ፡ ዝክተ ።

ወዝክተ ፡ ከብት ፡ አርብቶ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ገዝቶ ፡ መኖሩን ፡ እናደርጋለን ። አንድም ፡ ንገብር ፡ ዘንተ ፡ ከዚያች ፡ አገር ፡ መሄድን ፡ አው ፡ ዝክተ ፡ ወይም ፡ በዚች ፡ አገር ፡ መኖሩን ፡ እናደርጋለን ፡ ትሉ ፡ ይመስል ፡ ከማለት ፡ ወጥታችሁ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ሁሉ ፡ አነዋወራችሁ ፡ ምንድር ፡ ነው ። አንድም ፡ (ከመ ፡ እለ ፡ ይብሉ) ፡ ቢሆን ፡ ዘንድሮ ፡ ባይሆን ፡ ከርሞ ፡ ከዚያች ፡ ገዳም ፡ ሂደን ፡ (ንትጌበር) ፡ የርድናውን ፡ (ወንረብሕ) ፡ የተባሕትዎውን ፡ ሥራ ፡ ሠርተን ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ አግኝተን ፡ ተሹመን ፡ ከብረን ፡ እንኖራለን ፡ እንደ ፡ ሚሉ ፡ ከርሞ ፡ የሚሆነውን ፡ እንደማያውቁ ፡ ያች ፡ ገዳም ፡ ትፈታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አትፈታም ፡ እንደ ፡ ሆነ ። አንድም ፡ እነሱ ፡ ይሞቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይሞቱም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደማያቁ ፡ ሰዎች ፡ (ንገብር ፡ ዘንተ) ፡ ከዚያች ፡ ገዳም ፡ መሄዱን ፡ ወዝክተ ፡ የርድእናውን ፡ የተባሕትዎውን ፡ ሥራ ፡ መሥራቱን ፡ አንድም ፡ (ዘንተ) ፡ ከዚያች ፡ ገዳም ፡ መሄዱን ፡ አው ፡ ዝክተ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ መኖሩን ፡ እናደርጋለን ፡ ትሉ ፡ ይመስል ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ሁሉ ፡ ከማለት ፡ ወጥታችሁ ፡ አነዋወራችሁ ፡ ምንድር ፡ ናት ፡ የሐዋ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ።

፲፮ ፤ ወይእዜሰ ፡ ትትሜክሑ ፡ በምግባሪክሙ ፡

እንዲህ ፡ ሲሆን ፡ በሥራችሁ ፡ ትመካላችሁ ፡

ወዘኩሉ ፡ ትምክሕት ፡ እንተ ፡ ከመዝ ፡ እኪት ፡ ይእቲ ።

እንዲህ ፡ ያለችው ፡ ትምክሕት ፡ አጥፊ ፡ ናት ።

፲፯ ፤ ወዘሰ ፡ የአምር ፡ ገቢሮታ ፡ ለሠናይት ፡ ወኢይገብራ ፡

በጎ ፡ ሥራን ፡ ዐውቆ ፡ የማይሠራት ፡

ኃጢአተ ፡ ትከውኖ ።

ዕዳ ፡ ትሆንበታለች ። አንድም ፡ የሚመጸውተው ፡ ገንዘብ ፡ ሳለው ፡ የሚመጸውቱ ፡ ነዳያን ፡ ሳሉ ፡ የማይመጸውት ፡ ዕዳ ፡ ትሆንበታለች ። አንድም ፡ ጥበብ ፡ ተሰጥቶት ፡ አእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ቀንቶለት ፡ የሚበላው ፡ የሚጠጣው ፡ የሚለብሰው ፡ ሳያጣ ፡ የሚያስተምር ፡ መምህር ፡ ሳለ ፡ የማይማር ፡ ዕዳ ፡ ትሆንበታለች ። አንድም ፡ ግዕዛኑ ፡ ጸንቶለት ፡ ሀብተ ፡ ንጽሐ ፡ ተሰጥቶት ፡ ፀቱ ፡ ባሕርያት ፡ ተስማምተውለት ፡ የማይመነን ፡ ሰው ፡ ዕዳ ፡ ትሆንበታለች ፡ (ይሆንበታልም ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፵፯ ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ ፤ ንዑ ፡ ይእዜ ፡ አብዕልት ፡

ባለጸጎች ፡ ኑ ፡ ተሰብሰቡ ፡

ወብክዩ ፡ እንዘ ፡ ትግዕሩ ፡ ላዕለ ፡ ሕርትምናክሙ ፡ እንተ ፡ ሀለዋ ፡ ትምጻእክሙ ።

ትመጣባችሁ ፡ ዘንድ ፡ ባለች ፡ ጥፋታችሁ ፡ እየተጨነቃችሁ ፡ እዘኑ ፡ አልቅሱ ፤ ሐተታ ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ እንደ ፡ ወግዳ ፡ እንዲሉ ፡ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ አይቶ ፡ ሰውን ፡ ሰብስቦ፡ በሚያረዳ ፡ ሰው ፡ አምሳል ፡ ተናገረ ፡ ምሳ ፡ ፲፩ ፡ ፳፰ ። ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፳፩ ።

፪ ፤ ብዕልክሙኒ ፡ ነቅዘ ፡

እህሉን ፡ ነዳያን ፡ ኪበሉት ፡ ብላችሁ ፡ አኑራችሁት ፡ ነቀዝ ፡ በላው ፡

ወአልባሲክሙኒ ፡ ቈንቈነ ።

ልብሱን ፡ ነዳያን ፡ ኪለብሱት ፡ ብላችሁ ፡ አኑራችሁት ፡ ብል ፡ በላው ፡ ማቴ፡ ፮፡ ፲፱ ።

፫ ፤ ወርቅክሙኒ ፡ ወብሩርክሙኒ ፡ ዝሕለ ፡

ወርቁን ፡ ብሩን ፡ ነዳያን ፡ ኪወርሱት ፡ ብላችሁ ፡ አኑራችሁት ፡ ዛገ ፡

ወዛሕሉኒ ፡ ስምዐ ፡ ይከውን ፡ ላዕሌክሙ ፡

ዝገቱም ፡ መፈራረጃ ፡ ይሆንባችኋል ፡

ወይበልዖ ፡ ለሥጋክሙ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ በእንተ ፡ ዘገበርክሙ ፡ ለደኃሪ ፡ መዋዕል ።

ለኋላ ፡ ዘመን ፡ ይሆነናል ፡ ብላችሁ ፡ ስላኖራችሁት ፡ ፍቅሩ ፡ ሥጋችሁን ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ያቃጥሊዋል ። አንድም ፡ እሳት ፡ ሁኖ ፡ ያቃጥለዋል ፡ (ታሪክ) ፡ እንደ ፡ አባ ፡ ሠናየ ፡ ዝክር ፡(እንደ ፡ ባለ ፡ መቅጹት)፡ ድስት ፡ ምሉ ፡ ወርቅ ፡ ከራስጌው ፡ ዝልቅ ፡ አድርጎ ፡ ቆፍሮ ፡ ከዚያ ፡ ቀብሮ ፡ አኑሮ ፡ በተልእኮ ፡ ያመጡትን ፡ ሲመገብ ፡ ኑሯል ፡ በሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ ከራስጌው ፡ ዝልቅ ፡ አድርጎ ፡ ቆፍሮ ፡ ከዚያ ፡ ቀብሮ ፡ ልጆቼ ፡ የትሩፋት ፡ ደሜ ፡ የፈሰሰባት ፡ ናትና ፡ ከዚች ፡ ላይ ፡ ራሴን ፡ አድርጋችሁ ፡ ቅበሩኝ ፡ አላቸው ፡ እው ነት ፡ መስሏቸው ፡ ከዚያ ፡ ላይ ፡ ቀበሩት ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ እሳት ፡ ከመቃብሩ ፡ ላይ ፡ ሲጬስ ፡ ሲነድ ፡ ታየ ፡ አኀው ፡ ተሰ ብስበው ፡ የብቃት ፡ እንዳንለው ፡ ሁሉ ያይዋል ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ሲሉ ፡ አበ ፡ ማ በሩ ፡ ሰምቶ ፡ ቆፍሩት ፡ ብሎ ፡ ቢያስቆ ፍረው ፡ ወርቁ ፡ እሳት ፡ ሁኖ ፡ ሥጋውን በልቶ ፡ ራሱን ፡ ተያይዞት፡ ሕመት ፡ አድ ጎርት ፡ አክስሎት፡ ተገኝቷል፡ ዝ፡ ውእቱ ትእምርት ፡ ሾነኔ ፡ ገሃነም ፡ ዘድልው ለሰይጣን ፡ በዚህ ፡ ወርቅ ፡ ነዳያን ፡ ሊረ ዱበት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊታነጽበት አይገባም ፡ ብሎ ፡ ከባሕር ፡ አስጥሎታል ። አንድም ፡ በገሃነም ፡ ያቃጥለዋል ።

፬ ፤ ናሁ ፡ ዐስቦሙ ፡ ለገባር ፡ ለእለ ፡ ሐረስዋ ፡ ለም ድርክሙ ፡ ሄድክምዎሙ ፡ ወዐመፅክምዎሙ ፡ ዐስ ቦሙ ፡

ዐስቦሙና ፡ዐስቦሙ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ምን ፡ ሰምተህብናል ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ሆነ ፡ የገበራርት ፡ አምኟቸውን ፡ እነሆ ቀማችኋቸው ፡

ወእለኒ ፡ ሄድክምዎሙ ፡ የዐወይዉ ፡

አምኟቸውን ፡ የቀማችኋቸው ፡ ገበራ ትም ፡ ይጮሃሉ ።

ወገዓሮሙ ፡ ለዓፀድ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ እዘኒሁ ፡ ለእግ አብሔር ።

ጩኸታቸውም ፡ አቸናፊ ፡ ወደ ፡ ሚሆን ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጆሮ ፡ ደረሰ ዘዳግ ፡ ፳፬ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።

፭ ፤ ወበጽሐ ፡ ፍግዐክሙ ፡

ተድላ ፡ ደስታችሁ ፡ በዛ። አንድም ፡ ቦአ ፡ ወበጽሐ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡

ወፈጋዕክሙ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡

ተድላ ፡ ደስታ ፡ አደረጋችሁ ።

ወአስተትክሙ ፡

አስተትክሙን ፡ አቆይ ፡

ወተደለውክሙ ፡

ፈጋዕክሙ ፡ ወተደለውክሙ ፡ (ብለህ ፡ ግጠም) ፡ ተድላ፡ ደስታን ፡ አደረጋችሁ ።

ወአስባሕክሙ ፡ ልበክሙ ፡ ከመ ፡ ዘያሰብሕ ፡ ላህመ ፡ ለዕለተ ፡ ጥብሐት ።

ላምን ፡ ለሚያርዱበት ፡ ቀን ፡ እንዲያሰ ቡት ፡ ልቡናችሁን ፡ አሰባችሁ ፡ ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፲፱ ፡ ፳፫ ።

፮ ፤ ወተአደውክሙ ።

አስተትክሙ ፡ ወተአደውክሙ ፡ (ብለህ ፡ ግጠም) ፡ ኢታቢት ፡ ልብሶ ፡ ለዐሳብ ፡ እስመ ፡ አራዙ ፡ ይእቲ ፡ ባሕቲታ ፡ ያለ ውን ፡ አፈረሳችሁ ፡

ወቀተልክምዎ ፡ ለጻድቅ ።

ገበሬውን ፡ አምሾውን ፡ ነሥታችሁ ፡ በረሃብ ፡ ገደላችሁት ፡

ዘእንበለ ፡ ይትቃወምክሙ ።

ዳኛ ፡ አውጥቼ ፡ ዘንግ ፡ አቅንቼ ፡ ርስት ፡ ልካፈል ፡ ሳይላችሁ ፡

ወአሆ ፡ ይብለክሙ ።

የቆመውን ፡ ቁረጥ ፡ የወደቀውን ፡ ፍለጥ ፡ ብትሉት ፡ እሽ ፡ በጄ ፡ ሲላችሁ ። አን ድም ፡ (ወናሁ ፡ ዐስቦሙ) ፡ ቃላቸውን ፡ እንደ ፡ ገበሬ፡ ጸሎታቸውን ፡ እንደ፡ ዘርዕ፡ ሰውነታቸውን ፡ እንደ ፡ እርሻ ፡ አድር ገው ፡ የሚጸልዩላችሁ ፡ የነዳያንን፡ ትኳ ቧቸውን ፡ የቀማችኋቸው፡ ነዳያንም፡ ይጮ ሃሉ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ አንድ ፡ ነው ፤ (አስ ተትክሙ፡ ወተደለውክሙ)፡ እምሲሳይከ፡ አንከ ፡ አጽግቦ ፡ ለርኁብ ፡ እምእክልከ ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ አፈረሳችሁ ፡ (ወቀተ ልክምዎ)፡ ድኃውን፡ትኳቡን፡ ነሥታችሁ፡ በረሃብ ፡ ገደላችሁት ፡ (ጥቅ) ፡ ዝራዕ ፡ እክ ለከ ፡ ላዕለ ፡ መቃብረ ፡ ጻድቃን ፡ ዕደው ፡ ጻድቃን ፡ የሐልዉ ፡ ውስተ ፡ ምሳሕከ ፡ ወለእመ ፡ ኀጻበት ፡ እግረ፡ ጻድቃን ፡ እን ዲል። (ዘእንበለ ፡ ይትቃወምክሙ) ፡ ዳኛ፡ አውጥቼ ፡ ዘንግ፡ አቅንቼ፡ እህል ፡ በላዳን፡ ልከፈል ፡ ሳይል ፡ (ወአሆ) ፡ ባለ ፡ ቀን ፡ ያ ድርስህ ፡ ብትሉት፡ እሽ ፡ በጄ፡ እያላችሁ፡ ቀተልክምዎ ፡ ላለው ። አንድም ፡ (ወናሁ፡ ዐስቦሙ) ፡ ቃላቸውን ፡ እንደ ፡ ገበሬ ፡ ት ምህርታቸውን ፡ እንደ ፡ ዘርዕ ፡ ልቡናቸው ን ፡ እንደ ፡ እርሻ ፡ አድርገው ፡ የሚያስተ ምሯችሁ ፡ የመምህራንን ፡ የዕለት ፡ ምግባ ቸውን ፡ ከለከላችኋቸው ፡ (ወእለኒ) ፡ የዕለ ት ፡ ምግባቸውን ፡ የቀማችኋቸው ፡ መም ህራንም፡ ይጮሃሉ፡ ከዚህ፡ (በታች ፡ አይለ ወጥም)፡ (አስተትክሙ፡ ወተደለውክሙ)፡ ኢትፍጽም ፡ አፉሁ ፡ ለላሕም ፡ ሶበ ፡ ታ ከይድ ፡ እክለከ ፡ ይደልዎ ፡ ዐስቡ፡ ለዘይት ቀነይ ፡ ያለውን ፡ ሥርዐት ፡ አፈረሳችሁ ፡ (ወቀተልክምዎ) ፡ መምህሩን ፡ የዕለት፡ ራ ቱን ፡ ነሥታችሁ ፡ በረሃብ ፡ ገደላችሁት ፡ (ዘእንበለ ፡ ይትቃወምክሙ) ፡ ዳኛ ፡ አው ጥቼ ፡ ዘንግ ፡ አቅንቼ ፡ ወርቅ ፡ በሚዛን ፡ ልከፈል ፡ ሳይላችሁ ፡ (ወአሆ) ፡ ያልተመ ሰለውን ፡ መስለህ ፡ የተመሰለውን ፡ ተር ጕመህ ፡ ንገረን ፡ ብትሉት ፡ እሽ ፡ በጄ ፡ እያላችሁ ፡ ገደላችሁት ።

፯ ፤ ተዐገሡ ፡ እንከ ፡ አኀዊነ ፡ እስከ ፡ ደኃሪት ፡ ዕለት ፡ አመ ፡ ይመጽእ ፡ እግዚእክሙ ፡

ገበራርት ፡ መምራህን ፡ ነዳያን ፡ ጌታችሁ፡

www.ethiopianorthodox.org

እስከሚመጣባት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ታገሡ ፡

ከመ ፡ ሐረሳዊ ፡ ዘይጸንሕ ፡ ፍሬሃ ፡ ለምድር ፡ ክብርት ፡ እንዘ ፡ ይትዔገሣ ፡ ሠርከ ፡ ወነግሀ ፡ እስከ ፡ ትሰዊ ፡ ወትፌሪ ፡ ወትትዐፀድ ፡

እስክትሸትለት ፡ እስክታፈራለት ፡ እስክ ትታጨድ ፡ ድረስ ፡ የመዓልቱን ፡ ሐሩር ፡ የሌሊቱን ፡ ቊር ፡ ታግሦ ፡ የክብርት ፡ ምድር ፡ ፍሬዋን ፡ ደጅ ፡ እንደሚጠና ፡ ገበሬ ፡ ታገሡ ፡ (ሐተታ) ፡ ክብርት ፡ አላት ፡ አንዱን ፡ ቅንጣት ፡ ሠላሳ ፡ ስሳ ፡ መቶ ፡ ቅንጣት ፡ ታደርግለታለችና ፡ (ጥቅ)፡ ምድርኒ ፡ ታስተፌሥሖ ፡ ለሐራሲሃ ፡ በፍሬሃ ፡ ሶበ ፡ ትሁቦ ፡ ህየንተ ፡ አሐዱ ፡ ሠላሳ ፡ ወስሳ ፡ ወምእተ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ ጻብአ ፡ አጋንንትን ፡ ድምፀ ፡ አራዊትን ፡ ግርማ ፡ ሌሊትን ፡ ታግሦ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ክብር ፡ ደጅ ፡ እንደሚጠና ፡ ባሕታዊ ፡ መከራውን ፡ ታገሡ ።(ሐተታ) ሥራውን ፡ በሦስት ፡ ወገን ፡ ይሠሩታል ፡ በወጣኒነት ፡ በማዕከላዊነት ፡ በፍጹምነት ፡ ክብሩንም ፡ በሦስት ፡ ወገን ፡ ይወርሱታልና ፡ ትሰዊ ፡ ትፌሪ ፡ ትትዐፀድ ፡ አለ ፡ ሉቃ ፡ ፡ ፳፭ ፡ ፲፱ ። ዕብ ፡ ፲ ፡ ፴፮ ።

፰ ፤ ትዐገሡኬ ፡ አንትሙ ፡ ወአጽንዑ ፡ ልበክሙ ፡

ተዐገሡና ፡ ተዐገሡ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ልቡናችሁን ፡ በትዕግሥት ፡ አጽኑ ፡

እስመ ፡ ቀርበ ፡ ምጽአቱ ፡ ለእግዚእክሙ ።

ጌታችሁ ፡ የሚመጣበት ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ቀርቧልና ።

፱ ፤ ወኢትግዐሩ ፡ አኀዊነ ፡ ላዕለ ፡ ቢጽክሙ ፡

ገበራርት ፡ በጌቶች ፡ መምህራን ፡ በምእመናን ፡ ነዳያን ፡ በባለጸጎች ፡ አትዘኑ ።

ከመ ፡ ኢትትኰነኑ ፡

እንዳይፈረድባችሁ ፡ ፍርድስ ፡ የለም ፡ የተናሩት ፡ ዋጋችሁ ፡ እንዳይቀርባችሁ ፡ ማለት ፡ ነው ። አንድም ፡ ኢታግዕሩ ፡ ይላል ፡ ጌቶች ፡ ገበራርትን ፡ ምእመናን ፡ መምህራንን ፡ ባለጸጎች ፡ ነዳያንን ፡ አታሳዝኑ ፡ እንዳይፈረድባችሁ ፡ አሁን ፡ የተመቸ ።

እስመ ፡ ናሁ ፡ መኰንን ፡ ኀበ ፡ መድረከ ፡ ኆኅት ክሙ ፡ ይቀውም ፡ ወይጸንሕ ።

ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡ ኰናኒ ፡ በርትዕ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከደጃችሁ ፡ ቁሞ፡ ደጅ ፡ ይጠናልና ፡ ማለት ፡ ከደጅ ፡ የቆመ ፡ ግባ ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲገባ ፡ ፈጥኖ ፡ ይመጣልና ፡ ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፴፫ ።

፲ ፤ አርአያሃሰ ፡ አኀዊነ ፡ ለትዕግሥተ ፡ ተፅናስክሙ ፡ ብክሙ ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ ተናገሩ ፡ በቃሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

መከራውንስ ፡ ብንታገሥ ፡ ማን ፡ አብነት ፡ ይሆነናል ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታግሣችሁ ፡ ለምትቀበሉትስ ፡ መከራ ፡ አብነት ፡ የሚሆኗችሁ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተገልጾላቸው ፡ ትንቢት ፡ የተናገሩ ፡ ነቢያት ፡ አሉላችሁ ፡ እነሱ ፡ አብነት ፡ ይሁኗችሁ ፡

ናሁ ፡ ናስተበፅዖሙ ፡ ለእለ ፡ ተዐገሡ ፡

እነሆ ፡ መከራውን ፡ ታግሠው ፡ የተቀበሉ ፡ ነቢያትን ፡ እናመሰግናቸዋለን ፡ ብፁዕ ፡ ኤርምያስ ፡ ብፁዕ ፡ ኢሳይያስ ፡ ብፁዕ ፡ ኤልያስ ፡ እያልን ፡ ማቴ ፡ ፭፡ ፲፪ ።

፲፩ ፤ ወሰማዕክሙ ፡ ትዕግሥቶ ፡ ለኢዮብ ።

ብዙ ፡ ተናግሮ ፡ አንድ ፡ አመጣ ፡ የኢዮብንም ፡ ትዕግሥቱን ፡ ሰምታችኋል ። አንድም ፡ ታግሦ ፡ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ ሰምታችኋል ። አንድም ፡ በተቀበለው ፡ መከራ ፡ የተደረገለትን ፡ ሰምታችኋል ።

ዘከመ ፡ ፈጸመ ፡ ሎቱ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔር ፡ ትዕግሥቱን ፡ እንደ ፡ ፈጸመለት ፡ ሰምታችኋል ።

እስመ ፡ ብዙኅ ፡ ምሕረቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡

ወመስተሣህል ፡ ውእቱ ፡

ይቅርታውም ፡ ብዙ ፡ ነውና ። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ መሐሪ ፡ ነውና፡ ይቅር ፡ ባይም ፡ ነውና ፡ (ታሪክ) ፡ ኢዮብ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ። መዝ ፡ ፻፫ ፡ ፰ ።

፲፪ ፤ ወእምኵሉሰ ፡ ዘይቀድም ፡ አኀዊነ ፡ ኢትምሐሉ ፡

ወንድሞቻችን ፡ ከሁሉ፡ ግን፡ የሚቀድም። አንድም ፡ የሚበልጥ ፡ ነገር ፡ አትማሉ ፡

ኢበሰማይ ፡

በሰማይም ፡ ሆኖ ፡

ወኢበምድር ፡

በምድርም ፡ ሆኖ ፡

ወኢበካልእ ፡ መሐላ ፡

ኢበኢየሩሳሌም ፡ ባለው ፡

ኢትምሐሉ ፡ ግሙራ ፡

ከቶ ፡ አትማሉ ፡

ወኢበምንትኒ ፡

ኢበርእስክሙ ፡ ወኢበስእርተ ፡ ርእስክሙ ፡ ባለው ፡

አላ ፡ አሐደ ፡ ይኩን ፡ ቃልክሙ ፡

ነገራችሁ ፡ አንድ ፡ ይሁን ፡ እንጅ ፡

እመኒ ፡ እወ ፡ እወ ፡ ወእመኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ፡

ዕውነት ፡ ቢሆን ፡ ዕውነት ፡ ሐሰት ፡ ቢሆን ፡ ሐሰት ። አንድም ፡ ቢኖር ፡ አለ ፡ ባይኖር ፡ የለም ። አንድም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አለ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የለም ፡ ይሁን ፡ እንጅ ፡

ከመ ፡ ኢትትኰነኑ ፡

እንዳይፈረድባችሁ ፡

ወኢትባኡ ፡ ውስተ ፡ ደይን ።

ወደ ፡ ገሃነም ፡ እንዳትገቡ ፡ ማቴ ፡ ፭፡ ፴፬፤ ፵፰ ።

፲፫ ፤ እመ ፡ ቦ ፡ ዘይቴክዝ ፡ ለይጸሊ ፡

ቤት ፡ ንብረት ፡ አጥቶ ፡ የሚያዝን ፡ ቢኖር ፡ ከተድላ ፡ ሥጋ ፡ መከራ ፡ ይበልጣል ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ አንተ ፡ ለኔ ፡ ምቀኛዬ ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ ይለምን ፡ እንጅ ፡ የቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ኀዘን ፡ አይዘን ።

ወእመ ፡ ቦ ፡ ዘተፈሥሐ ፡ ለይዘምር ፡

ቤት ፡ ንብረት ፡ ከብት ፡ አግኝቶ ፡ ደስ ፡ ያለውም ፡ ሰው፡ ቢኖር፡ ባሕርዩ፡ ደካማ ፡ ነውና ፡ አይችልም ፡ ብለኸኝ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ለነፍስማ ፡ ከተድላ ፡ ሥጋ ፡ መከራ ፡ እንዲበልጥ ፡ ታውቆ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ያመስግን ፡ እንጅ ፡ አይመካ። አንድም፡ ሀብት፡ ሥርየት ፡ አጥቶ ፡ የሚያዝን ፡ ቢኖር ፡ ይለምን ፡ እንጅ ፡ የቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ኀዘን፡ አይዘን ፡ ሀብት ፡ ሥርየት ፡ አግኝቶ ፡ ደስ ፡ ያለውም ፡ ቢኖር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግን ፡ እንጅ ፡ አይመካ ፡ ማዝ ፡ ፺፡ ፲፭። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።

፲፬ ፤ ወእመ፡ ቦ፡ ዘይደዊ ፡ እምኔክሙ ፡ ለይጸውዕ ፡ ቀሳውስተ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ።

ከናንተ ፡ ወገን ፡ የታመመ ፡ ሰው ፡ ቢኖር፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የሚያገለግሉ ። አንድም ፡ በምእመናን ፡ ላይ ፡ የተሾሙ ፡ ቀሳውስትን ፡ ጠርቶ ፡ ይጸልዩለት ፡

ወይጸልዩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወይቅብዕዎ ፡ ቅብዐ ፡ ጸሎት ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አምነው ፡ መጽሐፈ ፡ ቀንዲል ፡ በዘይት ፡ ደግመው ፡ ይቅቡት ። አንድም ፡ ጸሎቱን፡

www.ethiopianorthodox.org

ቅሉ ፡ ቅብዕ ፡ አለው ፡ (ሐተታ) ፡ ለሰው ፡
የሚቀባ ፡ ራሱ ፡ ሳይቀምስ ፡ እጁ ፡ ሳይ
ነካ ፡ እንዳይቀር ፡ ለሰውም ፡ የሚጸልይ፡
ራሱን ፡ ሳይጠቅም ፡ አይቀርምና ፡
ማር ፡ ፮ ፡ ፲፫ ።

፲፭ ፤ ወጸሎት ፡ ሃይማኖት ፡ የሐይዎ ፡ ለድውይ ፡

እምነ ፡ የሚጸልዩት ፡ ጸሎት ፡ ድውዩን ፡
ያድነዋልና ፡

ወያነሥኦ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርም ፡ ያስነሣዋልና ፡

ወእመኒ ፡ ቦቱ ፡ ኃጢአት ፡ ይትኃደግ ፡ ሎቱ ።

ኃጢአትም ፡ ቢኖርበት ፡ ይሠረይለታል ፤
ሐተታ ፡ ኃጢአት፡ ሳይሠረይ ፡ ደዌ ፡ አይ
ርቅምና ፡ መዝ ፡ ፴ ፡ ፫ ።

፲፮ ፤ ተአመኑ ፡ በበይናቲክሙ ፡ ኃጢአተክሙ ፡

እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ኃጢአታችሁን ፡ ተጩ
ዋወቱ ፡ ተነጋገሩ ፡ (ሐተታ) ፡ የናዛዚው ፡
ባሕርይ ፡ ከተናዛዚው ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡
ነውና ። አንድም ፡ አንዱ ፡ ቄስ ፡ ላንዱ ፡
ቄስ ፡ ይነግረዋልና ። አንድም ፡ ኃጢአ
ቱን ፡ ለመምህረ ፡ ንስሓው ፡ መንገር ፡
ቢያፍር ፡ ለባልንጀራው ፡ ነግሮት ፡ ይንገ
ርለት ፡ ይላልና ፡

ወጸልዩ ፡ ላዕለ ፡ ቢጽክሙ ፡

ለወንድሞቻችሁ ፡ ጸልዩ ፡

ከመ ፡ ትሕየዉ ፡

ትድኑ ፡ ዘንድ ፡ ይሕየዉ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ።

ብዙኀ ፡ ትረድእ ፡ ጸሎቱ ፡ ለጻድቅ ፡

የጻድቅ ፡ ሰው ፡ ጸሎቱ ፡ ፈጽማ ፡ ታግዛ
ለች ፡ መደበኛ ፡ አትሆንምና ፡ ትረድእ ፡
አለ ፡ (ጥቅ) ፡ እመ፡ ቦ፡ ዘይስእል፡ ጸሎተ ፡
እምካልአኒሁ ፡ እንዘ ፡ ሐካይ ፡ በነፍሱ ፡
አልቦ፡ ዘይረብሖ፡ ወኢምንትኒ፡ እንዲል ፡

ትክል ፡ ወታስልጥ ።

ግዳጅ ፡ መፈጸም ፡ ይቻላታል ። ትክል ፡
ታሰልጥ ፡ ብሎ ፡ ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተና
ግሯል ፡ ለሁለቱም ፡ ያመጣል ።

፲፯ ፤ ኤልያስ ፡ ዘከማነ ፡ ሰብእ ፡ ውእቱ ፡

ኤልያስ ፡ እንደኛ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡

ወዘከመ ፡ ነሐምም ፡ የሐምም ፡

እኛ ፡ እንድንታመም ፡ ይታመም ፡ ነበረ ፡

ወጸሎተ ፡ ጸለየ ፡ ከመ ፡ ኢይዝንም ፡ ዝናም ፡

ዝናም ፡ እንዳይዘንም ፡ ሕያው ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አምላክ ፡ እስራኤል ፡ ዘቆምኩ ፡
ቅድሜሁ ፡ ከመ ፡ ኢይረድ ፡ ዝናም ፡ በ
እላ ፡ መዋዕል ፡ ዘእንበለ ፡ በቃለ ፡ አፉየ ፡
ብሎ ፡ ጸለየ ፡

ወኢዘነመ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ሠለስተ ፡ ዓመተ ፡ ወስ
ድስተ ፡ አውራኀ ።

ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ሰማይ ፡ ዝ
ናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ ምድርም ፡
የዘሩባትን ፡ ከማብቀል ፡ የተከሉባትን ፡
ከማጽደቅ ፡ ተከለከለች ፡ ተክል ፡ ላለው ፡
፩ ፡ ነገሥ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ። ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፳፭ ።

፲፰ ፤ ወካዕበ ፡ ጸለየ ፡ ከመ ፡ ይዝንም ፡

ዳግመኛም ፡ ዝናም ፡ ይዝነም ፡ ብሎ ፡
ጸለየ ፡

ወወሀበ ፡ ሰማይ ፡ ዝናሞ ፡ ወምድርኒ ፡ አብቈለት ፡
ፍሬሃ ።

ሰማይ ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡
ሰጠ ። ምድርም ፡ የዘሩባትን ፡ አበቀለች ፡
የተከሉባትን ፡ አጸደቀች ፡ ታሰልጥ ፡
ላለው ፡ ፩ ፡ ነገሥ ፡ ፲፰ ፡ ፵፪ ።

፲፱ ፤ አኀዊነ ፡ እመ ፡ ቦ ፡ ዘስሕተ ፡ እምኔክሙ ፡ እ
ምጽድቅ ፡

ወንድሞቻችን ፡ ከናንተ ፡ ወገን ፡ ከጽ
ድቅ ፡ ወጥቶ ፡ የበደለ ፡ ቢኖር ፡

ወእመ ፡ ቦ ፡ ዘሜጠ ፡ እምነ ፡ ጌጋዩ ።

መክሮ ፡ አስተምሮ ፡ ከበደሉ ፡ የመለሰው፡
ቢኖር ፡ ገላት ፡ ፮ ፡ ፩ ።

፳ ፤ ለያእምር፡ ከመ፡ አድኀነ፡ ርእሶ፡ እምነ፡ ሞት ፡

ራሱን ። አንድም ፡ ወንድሙን ፡ ከሞት ፡
እንዳዳነ ፡ ይወቅ ።

ወከደኖን ፡ ለብዙኃት ፡ ኃጣውኢሁ ፡

የራሱን ። አንድም ፡ የወንድሙን ፡ ብዙ ፡
ኃጢአቱን ፡ እንዳስተሠረየ ፡ ይወቅ ፤
ርእሶ ፡ ባለው ፡ ነፍሶ ፡ ይላል ፡ ነፍሱን ።
አንድም ፡ የወንድሙን ፡ ነፍስ ፡ እንዳዳነ ፡
ይወቅ ።

ተፈጸመት ፡ መልእክተ ፡ ያዕቆብ ፡ ሐዋርያ ፡ እኁሁ ፡
ለእግዚእነ ።

የጌታችን፡ ወንድም፡ ሐዋርያው፡ ያዕቆብ፡
የጻፋት ፡ ክታብ፡ ደረሰች ፡ ተፈጸመች ።

ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡

አስጀምሮ ፡ ላስፈጸመን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡
ምስጋና ፡ ይግባው ።

ኤልያስ ፡ ዝናም ፡ እንዳዘነመ ።

www.ethiopianorthodox.org